# የአንደኛ ክፍል የትውን እና የእይታ ጥበባት

## (የመምህሩ መምሪያ)



አዘጋጆች ፦ ምንያህል በቀለ
ደግፌ ጌታቸው
ካሌብ ካሳ

ስዕል ፦ ካሊብ ካሳ
ኖታ ቀራጭ ፦ ምንያህል በቀለ
ኤዲተር ፦ አምዶም ገ/ዩሃንስ

# ማውጫ


ምዕራፍ -1 **ምልከታ** ............................................................ 1

1.1.ከውዝዋዜ ጋር የተዛመዱ ቀላል መዝሙሮችን መስማት እና መመልከት ............................................ 4

1.2.ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ወይም ፎቶዎችን በማየት ድርጊቶችን መናገር .................................. 99

1.3. ምስሎችን ፣እንቅስቃሴዎችን እና መልዕክቶችን መረዳት ............................................ 11

1.4.**ቀጭንና ወፍራም ድምጽ መለየት** (pitch) ............................................ 18

ምዕራፍ- 2 **ፈጠራዊ አገላለጽ** ............................................ 23

2.1.የቤተሰብ አባላትን ተግባራት አስመስሎ መጫወት ............................................ 25

2.3. ስለ ቤተሰብ መዘመር ............................................ 40

2.4.ቀለል ባሉ ምቶች መወዛወዝ ............................................ 45

ምዕራፍ -3 **ባህሎች** ............................................ 54

3.1.አካባቢ እና ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጥበቦች ............................................ 57

3.2.በአካባቢያችን ያሉ ቀለሞች ............................................ 76

ምዕራፍ -4 **ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማድነቅ** ............................................ 83

4.1.የቤተሰብ መዝሙሮች ፣ውዝዋዜዎች ፣ሚና መጫዎት እና ምስል ............................................ 85

ምዕራፍ -5 **ትግበራ** ............................................ 101

5.1.በህብረት መዘመር ............................................ 102

5.2.በህብረት ሚና መጫዎት ............................................ 105

5.3.ስለ ተፈጥሮ ሃብት እና በዙሪያችን ስላሉ የተፈጥሮ ቀለሞች ............................................ 107

ከመዝሙሮች እና ምስሎች ጋር አቀናጅቶ መተግበር ............................................ 107

**መግቢያ**

ይህ የመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ የተዘጋጀው በአዲሱ የትምህርት መርሃ ትምህርት (ሲለብስ) መሰረት ነው፡፡

ይህ መጽሃፍ አዲሱን ትምህርት ስርዐት መሰረት በማድረግ ሙዚቃ፣ስዕል ፣ትያትር እንዲሁም ውዝዋዜን በአንድ ላይ በማካተት የትውን እና የእይታ ጥበባት በመባል ተዘጋጅቷል፡፡

የትውን እና የእይታ ትምህርት በአዲስ ይዘት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እርከን ድረስ ስለሚዘልቅ ያንን ታሳቢ በማድረግ ይሄ የአንደኛ ክፍል መጽሃፍ በትውን እና በእይታ ጥበቦች የመጀመሪያ መተዋወቂያ እንዲሁም ወደፊት ላሉት የክፍል ደረጃዎች መነሻ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

የሙዚቃን፣የስዕልን፣ የውዝዋዜ እና የትወና ጥበብን ሃገር በቀል ከሆኑ ባህል እና ልምዶች ጋር በማዛመድ እንዲተገበር በዚህ የአንደኛ ክፍል ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ የማስተማሪያ መጽሃፍ የተካተቱት ጥበቦች የራሳቸውን ገጽታ ሳይለቁ በራሳቸው በመቆም እንዲሁም እርስ በእርስ እንዲተጋገዙ ሆነው ለማስተማሪያነት ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህም መሰረት ይህ የአንደኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ ከተማሪዎች የመማሪያ መጽሃፍ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በአምስት ምዕራፎች ተዋቅሯል፡፡

**1.ምልከታ**

በዚህ ምዕራፍ ልጆች ስለ ተለያዩ እንቅስቃሴ እና መልዕክቶች ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ፣በፎቶግራፍ፣በስዕል እንዲሁም በመዝሙር በማገዝ እንዲገነዘቡ የሚደረግበት ነው፡፡

## 2.ፈጠራዊ አገላለጽ

በስዕል፣በሙዚቃ፣በውዝዋዜ እና በሚና መጫወት(ትወና) ልጆች የራሳቸውን የጥበብ ሙከራ የሚለማመዱበት ምዕራፍ ነው፡

## 3.ባህሎች

ልጆች ስለ አካባቢያቸው ባህል እና ልምድ በተለያዩ የጥበብ ውጤቶች የሚማሩበር እንዲሁም ባህላዊ ጥበቦችን የሚገነዘቡበት ምዕራፍ ነው፡

## 4.ባህላዊ ክንውኖችን ማድነቅ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ ድንቅ ባህሎችን በሙዚቃ፣በስዕል፣በትወና እና በውዝዋዜ በመታጀብ ስለ ባህሎቹ መልካሙን ነገር እንዲሁም ያለውን ዋጋ ይረዳሉ፡፡

## 5.ትግበራ

የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ እና ታሪካዊ ሃብት ሙዚቃን፣ስዕልን ፣ውዝዋዜን እንዲሁም ትወናን በአንድ ላይ በመተግበር የሚማሩበት ምዕራፍ ነው፡፡

## ተማሪዎች የዚህን የክፍል ደረጃ ሲጨርሱ ማወቅ የሚጠበቅባቸው ዋና ዋና ነጥቦች

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያለውን ድምፆች ፣ምስሎች እና ቀለሞችን ይለያሉ፡፡
- መዝሙሮችን እና ሚና መጫወትን ያሳያሉ፡፡
- ጥበባዊ ስራዎችነ ከአካባቢያቸው ይረዳሉ፡፡
- የጥበብ ስራዎንችን ያደንቃሉ፡፡

# ምዕራፍ -1
# ምልከታ

(ለምዕራፉ የተሰጠ  ክፍለ ጊዜ-25)

**መግቢያ**

የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምሰልን በመጠቀም የመማር ማስተማርን ሂደት  መተግበር አሁን ባለንበት አለም በስፋት እየተተገበረ የሚገኝ አንዱ የትምህር መርጃ ምንጭ ነው፡፡ የመማር ማስተማርን ሂደት በምስል እንዲሁም በድምጽ ማገዝ ለተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደት  ከፍተኛ የማነቃቃት እና የአሳታፊነት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በምስል እና በድምጽ የተደገፈ ትምህርት ለህጻናት ተማሪዎች ባለመሰልቸት ብዙ ሰዓትን ትምህርቱን እንዲከታተሉም ያግዛቸዋል፡፡

በብዙ ጥናቶችም እንደተረጋገጠው በክፍል የጽሁፍ ትምህርትን ለህጻናት ከማስተማር ይልቅ በምስል መደገፍ የልጆቹን ተሳታፊነት እንዲሁም ያዩትን ምስል ደግመው ለማስመሰል በሚያደርጉት ጥረት የትምህርቱን በውስጣቸው ዘላቂነት እንዲኖር ይረዳል፡፡

በምስልና በድምጽ  የታገዘ ትምህርት የልጆችን የመስማት እንዲሁም የመመልከት ክህሎት በከፍተኛ ሁኔታ ያዳብራል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ ልጆች የተለያዩ የድምጽ ፣የስዕል እና

የተንቀሳቃሽ ምስሎችን እንዲመለከቱ በማድረግ የተመለከቱትንም በራሳቸው እንዲገልጹ መርዳት ከመምህሩ(ሯ) ይጠበቃል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፡-**

- በተንቀሳቃሽ ምስል ያዩትን ከድምጽ ከምስል ጋር ያለውን መልዕክት ይገነዘባሉ፡፡
- የሰሙትን ድምጽ የድምጽ ደረጃ ይለያሉ፡፡በተጨማሪም የድምጹን ውፍረት እና ቅጥነት (high pitch and low pitch) ይለያሉ፡፡

  High pitch፡- የምንለው ከፍተኛ የድምጽ ቅጥነት ከፍታ ያላቸው ሲሆኑ

  Low pitch፡-የምንለው ደሞ ዝቅተኛ የድምጽ ቅጥነት ያላቸው ወፍራም ድምጾችን ነው፡፡
- በስዕሎች ያሉ መልዕክቶችን ተረድተው ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ይሞክራሉ
- የተመለከቷቸውን እንቅስቃሴዎች መልሰው በራሳቸው ለማሳየት ይችላሉ
- ስለተመለከቷቸው ስዕሎች እና ምልክቶች መግልጽ ይችላሉ

**የመማር ማስተማሪያ ግብዐቶች**

- የመለማመጃ በቂ ቦታ
- ስዕሎች

- ድምፅ ማጫዎቻ (በአካባቢው ሊገኙ የሚችሉ ድምጽ የሚያጫውቱ ግብአቶች)

ለምሳሌ፡-

ሬዲዩ ፣ቴፕ ማጫወቻ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ሲዲ ማጫወቻ፣ኮንፒውተር

- የተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻ መሳሪያ

(ለምሳሌ)

ቴሌቭዥን፣ቪዲዩ ማጫወት የሚችል ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ሲዲ ወይም ዲቪዲ ማጫወቻ፣ፕሮጀክተር፣ኮንፒውተር

- የህትመት ውጤቶች (ቻርቶች ፣ጋዜጣዎች፣መጽሄቶች፣መጽሃፎች፣ ወዘተ…
- የምልክት ቻርቶች ( በአካባቢያው የሚገኙ ምልክቶች)

**የማስተማሪያ ዘዴዎች**

- በድምጽ እና በምስል የታገዘ ማስተማር
- መልዕክት በምስል ማስተላለፍ
- የተማሪዎች የግል ስራ
- ሰርቶ የማሳየት ዘዴ
- የሚሰሩትን ስራ መምራት/መከታተል
- በመዝሙር ማስጠኛ (whole song methd or phrasal song method ) ማስጠናት

መዝሙሮች ቀላል እና አጭር ከሆኑ (whole song methd) እንጠቀማለን፡፡ የመዝሙሩን ሙሉ በአንድ ላይ ልጆችን ደጋግሞ ማዘመር፡፡

መዝሙሩ ረዥም እና ከባድ ከሆነ (Phrasal song method) ፍሬዝ በፍሬዝ ወይም መዝሙሩ ባሉት ፎርሞች ቅደም ተከተል አንዱን ፎርም ሲጨርሱ ሁለተኛውን ከዛም እንደ ቅደም ተከተሉ መዝሙሩን በመቆራረጥ ማስጠናት፡፡

**1.1.ከውዝዋዜ ጋር የተዛመዱ ቀላል መዝሙሮችን መስማት እና መመልከት** (ለርዕሱ የተሰጠ ጊዜ -8 ክፍለ ጊዜ)

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተመለከቱትን መዝሙሮች አስመስለው ይዘምራሉ
- የተመለከቱትን እንቅስቃሴዎች ያሳያሉ
- እንቅስቃሴ ያለባቸውን መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴ ጋር አስመስለው ያሳያሉ

**የመማር ማስተማሪያ ግብዓቶች**

- የመለማመጃ በቂ ቦታ
- ድምፅ ማጫዎቻ በአካባቢው ሊገኙ የሚችሉ ድምጽ የሚያጫውቱ ግብአቶች

ለምሳሌ፣

ሬዲዮ ፣ቴፕ ማጫወቻ፣ ስልክ፣ሲዲ ማጫወቻ፣ኮንፒውተር

- የተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻ መሳሪያ

ለምሳሌ፣

ቴሌቭዥን፣ቪዲዩ ማጫወት የሚችል ስልክ፣ሲዲ ወይም ዲቪዲ ማጫወቻ፣ፕሮጀክተር፣ኮንፒውተር

**ማነቃቂያ**

- ተማሪዎች የሚያውቁትን መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

ተማሪዎቹ በዚህ ክፍል እና እድሜ ሊያዮቸው የሚገቡ የተንቀሳቃሽ ምስል እና ድምጾችን ከእድሜያቸው ጋር ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

የተንቀሳቃሽ ምስሎቹ ህጻናት በግል በቡድን የሚከውኗቸው ጨዋታዎች፣መዝሙሮች ፣ውዝዋዜዎች ፣ተረቶች ፣እንቆቅልሾችን ሊያሳዩ ይገባል፡፡

መዝሙሮቹ በጣም ቀለል ያሉ የምት ምጣኔ ያላቸው እንዲሁም አጠር ያሉ ሊሆኑ ይገባል ይሄም የመዝሙር አጠናን ሶስቱን ዘዴዎች ያማከለ መሆን አለበት፡፡ እንቅስቃሴዎቹም በእድሜያቸው ሊተገበር የሚችል እና ቀላል እንቅስቃሴዎች መሆን አለባቸው፡፡

የድምጾችን ውፍረት እና ቅጥነት ከመረዳት ባለፈ ከበድ የሚሉ የሙዚቃ ጽንሰ ሃሳብ ማስተማር በዚህ ደረጃ ማስተማር አይገባም፡፡

በየእርዕሶቹ የቀረቡ አሳታፊ ጥያቄዎችን ልጆች እንዲመልሱ እንዲሁም ሃሳባቸውን በፈለጉት መንገድ እንዲገልጹ ማበረታታት ይገባል፡፡

**ስምሽ ማን ነው**

ስምሽ ማን ነው -ሰብለ ወንጌል

የት ትማሪያለሽ? -ጫሞ ትምህርት ቤት

መቼ ትመጫለሽ -ሰኞ ማታ

ምን ይዤልሽ -ቸኮላታ

ማርዬ ቻቻ ማርዬ ቻቻ ኦ እንጥሼ

**የመዝሙሩ ግጥም**

**ርዕስ፡- እንማር**

እንማር እንማር

እንመራመር

ለሃገር እንድንተርፍ

እንድንከበር

## እንማር (ዜማ፣ግጥም፡ ምንያህል)




## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- የሚያዳምጧቸውን መዝሙሮች በግል እንዲሁም በህብረት እስከ ሚያስታውሷቸው ድረስ ደጋግመው እንዲሰሙ ማድረግ
- ወፍራም ድምጽ እና ቀጭን ድምጽ ያላቸውን ድምጾች ከአካባቢ እንዲሰሙ ማድረግ
- በመጀመሪያ መዝሙሮችን እንቅስቃሴዎችን በተንቀሳቃሽ ምስል እንዲሁም በድምጽ እንዲያዳምጡ ማድረግ ካልሆነ መምህሩ መዝሙሮቹን እንዲሁም እንቅስቃሴዎችን አስመስሎ በራሱ ማሳየት ይገባል፡፡
- የሰሙትን የመዝሙር ግጥሞች በቃል እንዲናገሩ ተማሪዎችን ማሳተፍ

- ረዘም ያሉ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም መዝሙሮች ቢኖሩ መዝሙሩን ወይም እንቅስቃሴውን እንዲቀል በመከፋፈል አጠር አጠር አድርጎ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ማድረግ፡፡
- መዝሙሮች ስለ አካባቢው፣ስለ ጤና ፣ስለ ሃገር ፍቅር፣ስለ ቤተሰብ ፍቅር፣ ስለ ተፈጥሮ የሚያስረዱ እና የሚያስተምሩ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- የተለያዩ መዝሙሮችን ማሰማት….ከላይ የተሰጡትን መዝሙሮች በመጠቀም መጀመሪያ መዝሙሩን በማሰማት ግጥሙን እና መልዕክቱን ማስተዋወቅ ከዛ መዝሙሩን በሚገባ ማስጠናት፡፡መዝሙሮችን በቡድን ማስተግበር፡፡

## ክትትልና ግምገማ

- በመጽኃፋቸው ላይ ስለጨዋታዎቹ ያሉ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ማበረታታት፡፡
- የተመለከቷቸውን የድምጽ እና የተንቀሳቃሽ ምስሎች በትክክል መከታተላቸውን ማረጋገጥ
- የውዝዋዜ እንቅስቃሴዎቹ ለልጆቹ መስማማቱን ወይም መውደዳቸውን ማረጋገጥ
- የመዝሙር መልዕክቶችን መልሰው በቃል እንዲናገሩ በማድረግ መረዳታቸውን መገንዘብ
- በህብረት በመሆን እየተመለከቷቸውን ምስሎች እና እንቅስቃሴዎች መተግበራቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ወፍራም እና ቀጭን ድምጽ እንዲያወጡ ማበረታታት

## 1.2.ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ወይም ፎቶዎችን በማየት ድርጊቶችን መናገር (ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-5)

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማየት እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ
- በተንቀሳቃሽ ምስሎች ውስጥ ያለውን መልዕክት በአካባቢያቸው ካለው እንቅስቃሴ ጋር ያስተያያሉ
- ከምስሎቹ ውስጥ እንቅስቃሴ ያለባቸውን ከሌለባቸው ይለያሉ

### ለማስተማርያ ግብዐቶች

- ቴሌቭዥን፣ቪዲዮ ማጫወት የሚችል ስልክ፣ሲዲ ወይም ዲቪዲ ማጫወቻ፣ፕሮጀክተር፣ኮንፒውተር

### ማነቃቂያ ተግባር

- ከዚህ በፊት ስላዩት የቴሌቭዥን ወይም የሬዲዮ ፕሮግራም ወይም የመጽሃፍት ምስል እንዲናገሩ ማበረታታት


### ጠቃሚ መረጃ


በዚህ ርዕስ ላይ የተንቀሳቃሽ ምስል (የቴሌቭዥን ትምህርት መተግበር አይነተኛ መማሪያ አድርገን መውሰድ እንችላለን)የተማሪዎች መማሪያ ላይ ያሉትን ምስሎች እንደ ተጨማሪ ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል (በቴሌቭዥን )በመታገዝ

ትምህርቱ ካልተተገበረ እንደ ዋና ርዕሱን ማስተማሪያ መሆን ይችላሉ፡፡

ከታች በተሰጡት በሁለቱ ምስሎች ውስጥ የአካል እንቅስቃሴዎችን እናያለን በሶስተኛው ምስል ውስጥ ግን እንቅስቃሴ አለመኖሩ ከልጁ መተኛት እንገነዘባለን፡

**እንቅስቃሴ ያለባቸው እና የሌለባቸው ምስሎች**







## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎች በተንቀሳቃሽ ምስል የሚያዩአቸውን የተለያዩ ክንውኖች እንዲለዩ ማድረግ፡፡
- በምስሉ ውስጥ የተለያዩ ክንውኖች በተቻለ መጠን እንዲካተቱ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ የውዝዋዜ፣ የጨዋታ፣ የስራ ክንውንን የሚያሳዩ ምስሎችን ማካተት ፡፡
- ከዚህ በፊት እንደተመለከቱት አይነት እንቅስቃሴ ያለባቸው እና እንቅስቃሴ የሌለባቸውን ምስሎች ማሳየት፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መከታተላቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ልጆች የተመለከቱትን እንቅስቃሴዎች ለማስመሰል ቢፈልጉ ሳይከለክሉ በየተራ እንዲያሳዩ ማበረታታት፡፡
- ስለተመለከቱት እንቅስቃሴ በቃል እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በመጽሃፋቸው ላይ ስለጨዋታዎቹ ያሉ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ማበረታታት፡፡

## 1.3. ምስሎችን ፣እንቅስቃሴዎችን እና መልዕክቶችን መረዳት (ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-5)

## ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተመለከቱትን እንቅስቃሴዎች መልሰው ያሳያሉ፡፡

- ቀላል ምልክቶችን ይለያሉ፡፡
- የተደበቁ ምስሎችን ማግኘት ይገነዘባሉ፡፡
- ምልክቶች የያዙትን መልዕክት ይገልጻሉ
- የድምጽ ውፍረት እና ቅጥነትን ይረዳሉ፡፡

**የማስተማሪያ ግብአቶች**

- የተለያዩ ምልክቶችን የያዙ ምስሎች
- ተንቀሳቃሽ ምስልን ሊያሳዩ የሚችሉ መሳሪያዎች (ለምሳሌ ቴሌቭዥን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ)
- የተለያዩ መልዕክቶች የያዙ ስዕሎች

**ማነቃቂያ**

- መንገድ ላይ ያሉ የሚያውቋቸውን ፣ያዩአቸውን ምልክቶች እንዲናገሩ ማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

ለዚህ ክፍል በሚመጥን መልኩ ልጆች ምስሎችን እንዲገነዘቡ መርዳት ይገባል፡፡ የተለያዩ የምስል መልዕክት ማስተላለፊያዎችን መጠቀም እንችላለን ፡፡ እንዲሁም አካላዊ ምልክቶችም በራሳቸው የተለያዩ ትርጉም ኖሯቸው እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ የሰላምታ ምልክቶቸን በእጃችን ማሳየት ፣ እጅን ማውለብለብ ለሰላምታ፣ ሰው ሲመጣ ጎንበስ ማለት ክብርን ለመግለጽ እና ሌሎችንም ምልክቶች በምስል እንዲሁም በአካል በመተግበር ማሳየት ይገባል ፡፡ የውዝዋዜ እንቅስቃሴም ሊሆን ይችላል፡፡

## ምልክቶች የያዙትን መልዕክት መናገር



የእጆቻችንን ንጽህና መጠበቅ እንዳለብን የሚያሳይ ምስል

ቆሻሻን በአግባቡ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ብቻ መጣል እንዳለብን የሚጠቁም ምልክት



**ምልክቶችን ወይም ምስሎችን የሚለዩበት መንገድ**




ሁለት የተጨባበጡ ሰዎች መጨባበጥ መልዕክቱ ምን እንደሆነ መናገር፡፡መስማማትን፣ሰላምታን መወከሉን፡፡



ነጭ እርግብ የሰላም ምልክት እንደሆነ መግለጽ፡፡

ከታች የተመለከተውን  የሴት እና የወንድ ምስልን በማየት የትኛው የሴት የትኛው የወንድ እንደሆነ እንዲለዩ መርዳት



ምስሉ ላይ ምን እንዳዩ ልጆች እንዲያስረዱ ማድረግ ።



**የተደበቁ ምስሎችን ማግኘት መቻል**


ይሄ የስዕል እንቆቅለሽ አይነት ጨዋታ ነው ።ልጆች ፊት ለፊት ከሚታየው ምስል በተለየ የተጠየቁትን የተደበቀ ምስል ከሚያዩት ምስል ላይ ለይተው ያወጣሉ።

እንደዚህ አይነት ምስሎችን እንደ መነሻ በመውሰድ ልጆች በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሶችን ቁሶችን ከምስል ውስጥ እንዲለዩ የሚረዱ የምስል እንቆቅልሾችን ማዘጋጀት ከመምህሩ(ቷ) ይጠበቃል።



**በስዕሉ ላይ የሚታየው ባቢ ዓሣ ለመያዝ እየሞከረ ነው ፡፡ግን ዓሣ ማግኘት አልቻለም፡፡**

**አሳዎቹ ውሃ ውስጥ የሉም ፡፡አምስቱ ዓሣዎች የት ነው የሚገኙት? መልስ- ሁለቱ አሳዎች ከላይ ፣ሁለቱ በቀኝ በኩል፣አንዱ በግራ**



**ከምስሉ ውስጥ አሳ ይታያል፡፡**

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ❖ ተማሪዎች በመጽሃፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄ ያለባቸውን ምስሎች በቃል እንዲመልሱ ማድረግ ማበረታታት፡፡
- ❖ ተማሪዎች የተለያዩ ምስሎችን እንዲለዩ አንደኛው ምስል ከሌላኛም ምን አይነት ልዩነት እንዳለው እንዲረዱ ማድረግ፡፡
- ❖ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማስመሰል በአካል እንቅስቃሴ በማሳየት እንዲገነዘቡ ማስቻል፡፡
- ❖ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ያሉባቸው ምስሎችን በማዘጋጀት ምስሎቹ ላይ ያሉት እንቅስቃሴዎች የምን እንደሆኑ እንዲለዩ ማስቻል ፡፡ (ለምሳሌ የሚያጨበጭቡ ልጆች ያሚታበትን ምስል በማሳየት በምስሉ ላይ የልጆቹ ድርጊት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ እንዲሁም ድርጊቱን እንዲተገብሩት ማድረግ)
- ❖ በምስል የተደበቁ የእንቆቅልሽ ምስሎችን ለተማሪዎች ማስገንዘብ፡፡

### ክትትል እና ግምገማ

- ❖ ተማሪዎቹ በትክክል ምስሎቹን እንደተረዱ መመልከት
- ❖ በምስል የተመለከቷቸውን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የተመለከቷቸውን እንቅስቃሴዎች ስለምን እንደሆኑ መረዳታቸውን መከታተል

* ተማሪዎች ስላዩቸው ስዕሎች ተንቀሳቃሽ ምስሎች ድርጊቶች ወይም መልዕክቶች በግል እንዲሁም በቡድን እንዲገልጹ ማበረታታት
* በመጽሃፋቸው ላይ ያሉትን ጥያቄ ያለባቸውን ምስሎች በቃል እንዲመልሱ ማድረግ ማበረታታት፡፡

## 1.4.ቀጭን እና ወፍራም ድምጽ መለየት (pitch)

(ከርዕሱ የተሰጠ ክፍ ጊዜ-7)

ፒች ማለት የድምጽ ቅጥነት እና ውፍረት ደረጃ ማለት ነው፡፡ ድምጾች እንደ ምንጫቸው መለያየት የድምጾቹ ውፍረት እና ቅጥነትም ይለያያል፡፡

ሰዎች የተለያየ የድምጽ ውፍረት እና ቅጥነት አላቸው፡፡ እንደ አጠቃላይ ካየነው ወንዶች ወፈር ያለ ድምጽ ሲኖራቸው ሴቶች በአንጻሩ ቀጠን ያለ ድምጽ አላቸው፡፡በተለይ ይሄ የወንድ እና የሴት ድምጽ ልዩነት በደንብ የሚጎላው በጉርምስና ጊዜ ነው፡፡

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

* የወፍራም እና የቀጭን ድምጽ ልዩነት ይረዳሉ

### የማስተማሪያ ግብአቶች

* የተለያዩ የእንስሳት እና የሰዎች ድምጽ ቅጅዎች

❖ ተንቀሳቃሽ ምስልን ሊያሳዩ የሚችሉ መሳሪያዎች (ለምሳሌ ቴሌቭዥን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ)

**ማነቃቂያ**

❖ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ እንስሳት ሲጮሁ ወፍራም ድምጽ ያለውን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
ላም ፣በሬ ወፍራም ድምጽ ካላቸው ውስጥ እንመድባለን
ወፍ ፣ድመት ደሞ ቀጭን ድምጽ ካላቸው ውስጥ መጥቀስ እንችላለን

**ጠቃሚ መረጃ**

አእዋፍት ሲዘምሩ ድምጻቸው ቀጭን (high pitch )መሆኑ ይታወቃል ፡፡እንዲሁም እንደ ዝሆን ያሉ እንሰሳት ደሞ ድምጻቸው ወፍራም(low pitch or bass) ነው፡፡
ከፒች ጋር በተያያዘ ልጆች ላይ የድምጽ መጮህ እና የድምጽ ብዙ ያለ መጮህ (ዳይናሚክስ ) የሚለው ሃሳብ ከድምጽ መቅጠን እና መወፈር (ፒች) ጋር እንዳያምታታቸው መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ሃይ ፒች እና ሎው ፒች የሚለውን ወደ አማረኛ ስናመጣው የድምጽ ከፍታ ወይም ዝቅታ የሚል ትርጉም ከሰጠነው ከዳይናሚክስ ሃሳብ ጋር ይጋጫል ስለዚህ ፒች የሚለውን ቃል የድምጽ ቅጥነት እና ውፍረት ብሎ መተርጎም ተገቢ ነው፡፡

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ተማሪዎቸ በድምጽ ወፍራም እና ቀጭን ድምጽ እንዲሰሙ ማድረግ
- ወፍራም ድምጽ እንዲሁም ሌሎች ቀጭን ድምጽ ያላቸውን እንሰሳት ማሳየት፡፡
- ተማሪዎች የራሳቸውን ድምጽ በመጠቀም ወፍራም እና ቀጭን እያደረጉ የድምጽ ቅጥነት እና ውፍረትን እንዲረዱ ማድረግ ፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ልጆች የወፍራም ድምጽን እንዲሁም የቀጭን ድምጾችን መለየታቸውን ድምጽ እንዲያስመስሉ በማድረግ መመልከት
- ወፍራም ድምጽ ያላቸውን እንሰሳት በድምጽ እንዲሁም ምስላቸውን በማሳየት የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ልጆች በተንቀሳቃሽ ምስል እንዲሁም በምስል የተደገፉ ድርጊቶችን እና እንቅስቃሴዎችን እንዲረዱ ተደርጓል። እንቅስቃሴዎን የያዙ መዝሙሮችንም ተመልክተው ስለ እንቅስቃሴዎቹ መናገር እንዲችሉ ተደርጓል። መዝሙርን ፣እንቅስቃሴን ፣ድርጊቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች በዚህ ምዕራፍ የተተገበሩ ርዕሶች ናቸው። እነዚህን የምስል እና የእንቅስቃሴ መረዳት እውቀት ተማሪዎቸን ባሳተፈ ሁኔታ መምህሩ(ሯ) ተግብረዋል እንዲሁም ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የሙዚቃ አንዱ ባህሪ ሆነውን የድምጽ መወፈር አና መቅጠን ( pitch )ተረድተዋል ተብሎ ይታመናል።

**መልመጃ**

**(መምህሩ የሚጠይቃቸው የቃል ጥያቄዎች)**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለች መልሱ፡፡**

1. ውዝዋዜ በእንቅስቃሴ የሚገለጽ ድርጊት ነው፡፡
2. ምስሎች ወይም ምልክቶች መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡
3. መዝሙሮች መልዕክት የላቸውም፡፡
4. በመዝሙር መወዛወዝ ይቻላል፡፡
5. የበሬ ድምጽ ከድመት ድምጽ ይወፍራል፡፡

**መልስ**

1.እውነት 2.እውነት 3.ሐሰት 4.እውነት 5. እውነት

# ምዕራፍ- 2
## ፈጠራዊ ገለጻ

(ለምዕራፉ የተሰጠ ጊዜ -30 ክፍለ ጊዜ)

### መግቢያ

ስዕል፣ጽሁፍ ፣ትወና (ሚና መጫዎት)፣ሙዚቃ መጫዎት ፣ማቅለም እንዲሁም የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን መስራት ጥበባዊ ገለጻዎች ( creative expression) ናቸው።

ጥበባዊ ገለጻዎች ለህጻናት የማወቅ ፍላጎትን በመጨመር ጥልቅ ሰሜትን በማስረጽ የፈጠራ ችሎታቸውን ያሳድጋል።

ለአንድ ልጅ ስዕል እንዲስል ወይም አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ብንሰጠው ልጁ እራሱን በጥበብ ለመግለጽ መሞከሩ እሙን ነው ። ይህም እራሱን የመግለጽ አቅም እየጎለበተ የፈጠራ ችሎታንው ያጎለብታል።

የጥበባዊ ገለዎች ህጻናት ስለ አካባቢያቸው ያላቸውን መረዳት በማሳደግ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን፣መረዳታቸውን፣ የመነቃቃት ስሜትን ይጨምራል።

ለጥበባዊ ገለጻም ልጆች ሰፋ ያለ እና ያልተፋፈገ ቦታ እና አካባቢ ያስፈልጋቸዋል።ይሄንን በመረዳት ለልጆች ጥበባዊ ገለጻ አስፈላጊ እና ተስማሚ በሆነ መልኩ ቦታዎችን ፣ቁሶችን፣እና ጊዜን ማስተካከል ከመምህራን ይጠበቃል።

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፡-**

- የተለያዩ ሚናዎችን በትወና ጥበብ ማሳየት ይችላሉ
- የተለያዩ መስመሮችን እና ቀላል ንድፎችን በመሳል ያሳያሉ
- ስለ ቤተሰብ የሚያወሱ  መዝሙሮችን ይዘምራሉ
- ቀላል የውዝዋዜ እንቅስቃሴዎችን መተግበር ይችላሉ

**የማስተማሪያ ግብአቶች**

- የመለማመጃ ስፍራ
- የድምጽ እና የተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻ መሳሪያ (ቴሌቭዥን ወይም ኮንፒውተር ካልተገኘም ተንቀሳቃሽ ምስል ማሳየት የሚችን ተንቀሳቃሽ ስልክ)
- የምት የሙዚቃ መሳሪያ (ከበሮ፣አታሞ ወዘተ…)
- የተለያየ የድምጽ ደረጃ  (pitch) ሊያወጡ የሚችሉ መሳሪያዎች (ክራር፣ማሲንቆ፣ዲታ ወዘተ…)
- የድምጽ ወይም የምስል ቅጅዎችን የያዙ ካሴቶች ወይም ሚሞሪ ካርዶች
- እርሳሶች ባለቀለም መጻፊያዎች ወይም ለመጻፊያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ በአካባቢያችን የሚገኙ ቁሶች

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የሚና ጨዋታ
- መልዕክት በምስል ማስተላለፍ

❖ የተማሪዎች የግል ስራ

❖ የተማሪዎች የቡድን ስራ

❖ ሰርቶ የማሳየት ዘዴ

❖ የሚሰሩትን ስራ መምራት/መከታተል

❖ በመዝሙር ማስጠኛ

whole song methd -አጭር እና ቀላል መዝሙሮችን ሙሉውን ደጋግሞ በማሰማት ማስጠናት

phrasal song method -ረዘም ያሉ መዝሙሮችን በመቆራረጥነ ስንኝ በስንኝ ) ማስጠናት

## 2.1.የቤተሰብ አባላትን ተግባራት አስመስሎ መጫወት ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-7)**

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

❖ የቤተሰቦቻቸውን ተግባራት አስመስለው መጫወት ይችላሉ

❖ የቤተሰብ አባላትን ተግባራት እንዲሁም የስራ ድርሻ ይገነዘባሉ

❖ በእንቅስቃሴ መልዕክት የማስተላለፍ ክህሎትን ያዳብራሉ

❖ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያላቸውን መልዕክት ይረዳሉ

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

❖ ለመለማመጃ እና ለአስመስሎ መጫዎቱ የሚሆን በቂ ስፍራ

- የተለያዩ ገጸ ባህሪዎችን አስመስለው ለመጫዎት የሚረዱ ቁሳቁሶች (አልባሳት፣በእጅ የሚያዙ መገልገያ መሳሪያዎች)
- ተንቀሳቃሽ ምስል ( video) ማጫወቻ ቁሶች

**ማነቃቂያ**

- የቤተሰቦቻቸውን የቤት ውስጥ ሚና እንዲናገሩ ማበረታታት

**ጠቃሚ መረጃ**

ለልጆች አንድን ድርጊት አስመስሎ መተግበር የትግበራ እና አንድን ነገር የማድረግ ችሎታን በከፍተኛ ሁኔታ የማያሳድግ ቁልፍ ተግባር ነው። አስመሎ መጫወት ለልጆች ነገሮችን በፍጥነት የመረዳት አቅማቸውን ይጨምራል። ልጆች እንቅስቃሴን (ለምሳሌ መራመድን ፣ መሮጥን ፣ መቀመጥን ፣መነሳትን) ፣ ንግግርን በመጀመሪያ የሚማሩት የቅርብ የቤተሰብ አባሎቻችውን አስመስለው ለመጫዎት በሚያደርጉት ሙከራ ነው።

በዚህም የትምህርት ጊዜ ልጆች የተለያዩ የቤተሰብ አባሎቻቸውን በመወከል ይተውናሉ። መጀመሪያ ልጆች ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስመስሉ የሚጠበቀውም ለማንኛውም ህጻን የመጀመሪያ መምህሮቹ ቤተሰቦቹ (ወላጆቹ )በመሆናቸው ነው።በመጀመሪያ አንድ ሀጻን አመጋገብን ፣ንግግሩን ፣ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት፣ እንዲሁም ሌሎች ክህሎቶችን ከቤተሰቡ ከተማረ በኋላ ነው በመቀጠል ሌሎች ክህሎቶችን ወደ መማር የሚሸጋገረው።

## መነሻ ሃሳብ-አንድ

ልጆች ብዙ ጊዜ የቤተሰቦቻቸውን ድርጊት በተለምዶ እቃቃ በምንለው አይነት ጨዋታ ሲተገብሩ ማየት የተለመደ ነው፡፡ይሄንን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸው ቤት ውስጥ የሚተገብሩትን እንዲያስመስሉ ማድረግ፡፡ ከነዚህም የቤተሰብ አባል ክንውኖች ውስጥ ልጆችን መንከባከብ አንዱ ተግባር ነው፡፡

ተማሪዎች አንድ አሻንጉሊት በመውሰድ ቤተሰቦቻቸው እንደሚያደርጉት ሲንከባከቡ፣ሲመግቡ፣ሲያጫውቱ፣ወደ ትምህርት ቤት ሲወስድ ያለውን ድርጊት አስመስለው እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡ለዚህ የማስመሰል ጨዋታ ልጆች ከተቻለ እንደ ቤተሰባቸውን አለባበስ እንዲለብሱ መርዳት፡፡

## መነሻ ሃሳብ -ሁለት

በአካባቢው ቁሳቁሶች ባይኖሩም መምህሩ አንድ አባትን ወክሎ በግቢው አትክልቶችን ሲነከባከብ እና ሲያጠጣ የሚያሳይ የቤተሰብ አባልን ወክሎ መጫዎትን ማሳየት ይችላል ፡፡ እንቅስቃሴዎቹ በምልክት ሲኮተኩት፣ በጎማ አትክልቶችን ውሃ ሲያጠጣ፣ እንዲሁም አትክልቶችን ሲተክል ሊሆን ይችላል፡፡እንደ ምሳሌ ወይም እንደ መነሻ ልጆች እንዲወስዱት ማድረግ ይቻለል፡፡

የእናት የአባቶቻቸውን ንግግር እንዲሁም ከእነሱ ጋር የሚያደርጉትን የቃላት ምልልስ አስመስለው እንዲጫወቱ ማድረግ ይቻላል፡፡

ድርጊቶቻቸውን ብቻ ሳይሆን የፊት ገጾቻቸውንም በመጠቀም የመደሰት ፣የመድከም፣የመደነቅ ስሜቶቻቸውንም አካተው እንዲጫወቱ ማድረግ ይገባል፡፡

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ❖ በመጀመሪያ አንድ ገጸ ባህሪን መምህሩ ተጫውቶ በማሳየት ልጆቹ እንደመነሻ ሃሳብ እንዲይዙ ማድረግ፡፡
- ❖ በመጀመሪያ አስመስለው የሚጫወቱትን አካል ወይም የቤተሰብ አባል መግለጽ እንዲሁም ስለ ሚጫወቱት የቤተሰብ አባል አንድ አንድ መግለጫ መስጠት፡፡
- ❖ እንዲሁም ተመሳሳይ ገጸ ባህሪ በመስጠት ሁሉም ልጆች በራሳቸው መንገድ አንድን ገጸ ባህሪ እንዲጫወቱ ማድረግ ፡፡ለዚህ ትግበራ እንደ መነሻ የሚጫወቱትን ሚና ማሳየት፡፡
- ❖ የትኛው ተማሪ ሚናውን በአግባቡ እንደተወጣ እራሳቸው ልጆች እንዲለዩ ማድረግ፡፡

**ክትትል እና ግምገማ**

- ❖ ተማሪዎች ሚና መጫዎትን በትክክል ገብቷቸው መተግበራቸውን መመልከት፡፡
- ❖ ሚና መጫወት ትምህርቱ በሁሉም ህጻናት መተግበሩን መከታተል፡፡
- ❖ ልጆች የተጫወቱትን ሚና በንግግር እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

## 2.2. መቸክቸክ ፣መስመር፣ ቅርጾች መለማመድ እንዲሁም ማቅለም (ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-8)

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- መስመር በመቸክቸክ የጣት እንቅስቃሴያቸውን ያስተካክላሉ
- መስመር በማስመር የተለያዩ ቅርጾችን መስራት ይችላሉ
- ቀለም እና ንድፎችን ይለያሉ፡፡
- ቀለል ያሉ ንድፎችን ይነድፋሉ፡፡
- ቅርጾችን ይለያሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ወረቀቶች
- መጻፊያ እርሳሶች፣እስኪርቢቶዎች፣ባለቀለም መጻፊያዎች
- በአካባቢ ሊገኙ የሚችሉ መጻፊያ መሳሪያዎች(ለምሳሌ ከሰል)
- ቀለም መቀቢያ ብሩሽ (ወይም የሚገኝ ቀለም መቀቢያ)
- ላጲስ ፣መቅረጫ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ልጆች የፈለጉትን አይነት መስመር ወይም ምስል ደጋግመው እንዲሰሩ ማበረታታት

## ጠቃሚ መረጃ


ለተማሪዎች የወደፊት የፈጠራ እና የመጻፍ ችሎታ መስመሮችን መስራት እና መቸክቸክ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው በመረዳት ልጆች በትክክል እንዲተገብሩት መርዳት ያስፈልጋል፡፡ልጆች በሚቸከችኩበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ በሶስት ቅርጾች መሰረት እንዲተገብሩ ማድረግ፡፡ መጽሃፋቸው ላይ እንዳይቸከችኩ መለማመጃ መጽሃፍ እንዲያዘጋጁ እና እዛ ላይ እንዲተገብሩ ማድረግ ይገባል፡፡

## 2.2.1. መቸክቸክ


መቸክቸክ ማለት በእርሳስ እንዲሁም በሌላ መጻፊያ እጅን ወደ ፈለጉት አቅጣጫ በማስኬድ የተለያዩ መስመር መሰል እና እጥፋቶች መስራት ማለት ነው፡፡

ልጆች መቸክቸክ እጃችሁ በደንብ ስዕል ለመሳል ፣ለመጻፍ እንዲፍታታ ያደርግላችኋል፡፡


**ወደ ጎን (አግድሞሽ )መቸክቸክ**



I. **ወደ ታች የሚወርድ መቸክቸክ**



II. **ክብ መስመሮችን በሚሰራ መልኩ መቸክቸክ**



**ሶስቱን ችክቸካዎች ከተለማመዱ በኋላ ሶስቱንም አንድ ላይ እንዲተገብሩ በማድረግ ይበልጥ ተማሪዎቹ እጃቸውን እንዲያፍታቱ ማድረግ፡፡**

**ለተማሪዎቹ በሚመጥን እና ተስማሚ እና ፍላጎታቸውን ባማከለ ሁኔታ ትምህርቱን መስጠት ከመምህሩ(ሯ) ይጠበቃል፡፡**

**የመቸክቸክ ተጨማሪ ምሳሌዎች ልምምድ ምሳሌዎቸ**

ልጆች እጃቸውን በመቸክቸክ ካፍታቱ በኋላ ከዚህ በታች ያሉትን መስመሮች እና ቅርጾች ማስተማር ይቻላል፡፡

### 2.2.2. የመስመር ንድፍ መለማመድ

መሰረታዊ የመስመር ዓይነቶች

**ቋሚ መስመር**


ከላይ ወደ ታች የሚወርድ ቀጥ ያለ መስመር

**አግድም መስመር**

ከመሬት ጋር ትይዩ የሚሄድ መስመር (ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀይ ወደ ግራ የሚሰመር ቀጥ ያለ መስመር)


**ሰያፍ መስመር**

ቀጥ ያለ ሆኖ በግማሽ የወደቀ መስመር



**ታጣፊ ወይም ቆልማማ መስመር**

የክብ መስመር ተቆርጦ የወጣ መሳይ መስመር




**ዚግዛግ መስመር**

የሰያፍ መስመሮች ስራት ሲሆን የተቆራረጠ ውጣ ውረድን የሚያሳይ መስመር ነው




**የሞገድ መስመር**

ቆልመም ባለ መታጠፊያ ከፍ ዝቅ የሚል መስመር



**ሽክርክር መስመር**

ደጋግሞ የሚዞር መስመር




## 2.2.3.ለልጆች መሰረታዊ ቅርጾች

ልጆች በመሰረታዊነት ሊያውቋቸው የሚገቡ ቅርጾች፡፡


### እኩል አራት ማዕዘን ቅርጽ

በአራቱም ጎን ያሉ መስመሮች እኩል ልኬት ይኖራቸዋል




### አራት ጎን ያለው ቅርጽ

አራት ጠርዝ ያለው ቅርጽ ነው፡፡ ቋሚ እና አግዳሚው መስመር እኩል ልኬታ የላቸውም፡፡




**ክብ ቅርጽ**

**አንድ መስመር በሶስት መቶ ስልሳ ዲግሪ ዞሮ ሲገጥም ክብ ቅርጽ እንላለን፡፡**




**ሞላላ ቅርጽ**

እንደ እንቁላል አይነት ሞለል ያለ ክብ ቅርጽ መሳይ ነው፡፡




**ሶስት ጎን ያለው ቅርጽ**

ሶስት መዐዘን ቅርጽ ሶስት ጠርዞች ያሉት መስመር ነው፡፡




## አምስት መዐዘን የያዘ ቅርጽ

አምስት ጠርዞች ያሉት ቅርጽ ነው፡፡




## የኮከብ ቅርጽ



## 2.2.4.ቅርጾችን ማቅለም

ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ቅርጾች ከተለማመዱ በኋላ የቅርጾቹን ውስጥ በእርሳስ ፣ በእስኪርቢቶ፣ በአካባቢያቸው ሊገኙ ከሚችሉ  ባለቀለም የመጻፊያ መገልገያዎችን  በመጠቀም እንዲያቀልሙ  ማድረግ፡፡(ለምሳሌ ተክል ቅጠሎችን ፣ከሰል፣ቾክ )

**ምሳሌ**



**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- የሚቸከችኩትን የመስመር ወይም የቅርጽ ሁኔታ በተግባር ማሳየት ::
- የልጆች የእርሳስ ወይም የመጻፊያ አያያዛቸውን በሚመቻቸው እና ተገቢ በሆነ መንገድ እንዲይዙ መምህሩ(ሯ) ማሳየት ::
- ልጆች በደንብ እጃቸውን እንዲያፍታቱ የተለያዩ መስመሮችን ወይም መቸክቸኮችን ደጋግመው እንዲለማመዱ ማድረግ::
- ተማሪዎቹ የተለያየ መስመሮችን በስያሜ እንዲለዩ ማድረግ::

- ነጠብጣብን በመጠቀም የተማሪዎች መማሪያ ላይ ርዕስ (2.2.3) ላይ ባለው መለማመጃ መስመር ማሰራት ፡፡
- ልጆች የፈለጉት አይነት መስመር ወይም ንድፍ እንዲነድፉ ማበረታታት፡፡
- መስመሮችን በመጠቀም የተለያዩ ቅርጾችን እንዲሰሩ መርዳት፡፡
- በሰውነታቸው መስመሮችን እንዲሰሩ ማበረታታት፣ቅርጾችን እለት ከእለት ከምንገለገልባቸው ቁሶች ጋር ማገናኘት፡፡
- ለምሳሌ ሳጥን አራት ማዕዘን እንደሆነ ፣እንቁላል ሞላላ ቅርጽ እንደሆነ ፡፡መስመሮችንም በመቆም በማጎንበስ መስመሮችን መስራት፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- መምህሩ የተማሪዎችን መስመር የማስመር የመቸክቸክ፣ቅርጾችን የማቅለም ስራ ይመለከታል
- ልጆች ስለ ተማሩት መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ
- በቡድን ሆነው መስመሮችን ወይም ቅርጾችን መስራታቸውን ማረጋገጥ
- በተሻለ እንዲሰሩ የሁሉንም ስራ ማድነቅ እና የተሻለውን እንደ ምሳሌ መጠቀም

❖ በተማሪ መማሪያ ላይ ያሉ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ስለ ቅርጾች ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ቁሶችን ቅርጾች እንዲያውቁ ማበረታታት፡፡

## 2.3. ስለ ቤተሰብ መዘመር

(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-7)

**ከርእሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

❖ ልጆች የተለያዩ ስለቤተሰብ የተዘመሩ መዝሙሮችን መዘመር ይችላሉ፡፡

❖ ልጆች በቡድን በመሆን ድምጻቸውን በህብረት በማስተካከል ለመዘመር ይሞክራሉ፡፡

❖ ስለቤተሰቦቻቸው ፍቅር ለሌሎች ተማሪዎች ይገልጻሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

❖ የድምጽ ማጫወቻ መሳሪያ(ቴፕ፣ድምጽ የሚያጫውት ስልክ)

❖ የመዝሙር ግጥሞች፡፡

❖ በድምጽ መቅጃ(በካሴት) የተቀዱ አካባቢያዊ ስለቤተሰብ የሚያወሱ መዝሙሮች፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ❖ ልጆች አንድ የሚያውቁትን መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

መዝሙር ልጆች በግል ወይም በጋራ ሲዘምሩ ደስታን እንዲሁም መዝናናትን ከመስጠት ባሻገር አካላዊ እንዲሁም አይምሯዊ ብስለትን ያጎናጽፋል፡፡

ተማሪዎች ስለቤተሰብ የሚያወሱ ቀለል ያሉ መዝሙሮችን በሚያጠኑበት ግዜ ለልጆቹ ተስማሚ የሆነ የመዝሙር ማጥኛ ዘዴ መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ርዝመት ያላቸው መዝሙሮችን እንዲሁም ከበድ ያሉ የምት አይነት ያላቸውን መዝሙሮች መጠቀም አይገባም፡፡

አጠር ብለው ግን ልጆች በቀላሉ ሊይዟቸው ካልቻሉ ግጥሙን ሃረግ በሃረግ ማስረዳት ተገቢ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ❖ የመዝሙሩን ግጥም መጀመሪያ በቃል እንዲይዙት ማድረግ ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡
- ❖ ልጆች መዝሙሮችን እንዲዘምሩ ማበረታታት፡፡
- ❖ መዝሙሮቹን በግል እና በህብረት እንዲተገብሩ መርዳት፡፡
- ❖ ሌላኛው ልጆች በሚዘምሩበት ግዜ ዳኝነት መስጠት ወይም መዝሙሩን በትክክል ባይሉት ልክ እንዳልሆኑ ከመንገር ይልቅ ድግግሞሽ በማድረግ ልጆች በትክክል መዝሙሩን እንዲዘምሩ መርዳት፡፡

**የመዝሙር ማስጠኛ ዘዴዎች በዋናነት ሶስት ናቸው፡፡**

1. የሙሉ መዝሙር አጠናን
2. ሃረጋዊ የመዝሙር አጠናን
3. ሁለቱንም ያጣመረ የመዝሙር አጠናን ናቸው፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ መጠቀም ተመራጭ የሚሆነው የሙሉ መዝሙር አጠናን ዘዴን ነው ፡፡ይህውም የምናዘምረው መዝሙር አጭር እና ቀላል ስለሆነ ነው፡፡

ሙሉ የመዝሙር አጠናን ማለት መዝሙሩን በሙሉ እየደጋገሙ ልጆች በቃላቸው እስኪይዙት ድረስ ማስደመጥ ነው፡፡

**ስለ ቤተሰብ የሚያወሱ መዝሙሮች**

**የቤተሰብ መዝሙር ግጥም**

ከስር የተገለጸውን ግጥም መምህሩ በፈለገው ዜማ ወይም አካባቢው ላይ ከሚገኝ ከሌላ የመዝሙር አይነት ዜማ በመቅዳት እንደዚህ አይነት ስንኝ ያላቸውን መዝሙሮች መፍጠር ይገባዋል(ታል)፡፡

**እወዳችኋለሁ**

አባ.......ቴ

እና......ቴ

ወንድሜ እህቴ

እውዳችኋለሁ ከራሴ አብልጬ

በአካባቢያችን  የተለመዱ ስለ ቤተሰብ የሚናገሩ መዝሙሮችን በቀላሉ ማግኘት የማይቻል ከሆነ ልጆቹ የራሳቸውን የቤተሰብ አባል ስም በማስገባት ከዚህ በፊት በሚያውቋቸው የልጆች መዝሙሮች ግጥሞች ውስጥ በመተካት እንዲዘምሩ  ማለማመድ አንዱ ዘዴ ነው፡፡

ቀጥሎ በብዙ ህጻናት የሚወደደውን ወንድሜ ያዕቆብ የሚለውን መዝሙር ማዘመር ፡፡

**ወንድሜ ያዕቆብ**

ወንድሜ ያዕቆብ
ወንድሜ ያዕቆብ
ተኝተሃል ወይ
አትነሳም ወይ
ደውል ተደወለ
ደውል ተደወለ
ተነሳ    ተነሳ
እህቴ የሺ
እህቴ የሺ
ተኝተሻል ወይ
አትነሻም ወይ
ደውል ተደወለ
ደውል ተደወለ
ተነሺ    ተነሺ

## ስለቤተሰብ የሚገልጽ መዝሙር

## እንዴት ነሽ

.

.

*የወንድሜ  የእህቴ  ጓደኛ*

*እንዴት ነሽ እንዴት ነሽ  ንገሪኛ*



## እናቶች ልጆቻቸውን ለማስተኛት ሚጠቀሙበት ባህላዊ መዝሙር

### እሹሩሩሩ

እሹሩሩሩ እሹሩሩሩ
የማሙዬ እናት ቶሎ ነይ ለት
ወተቱን በጉያ
ዳቦውን ባህያ
ይዘሽለት ነይ እሹሩሩሩ

### ክትትል እና ግምገማ

- የመዝሙሩን ግጥም በትክክል በቃል ማለታቸውን መከታተል።
- የመዝሙሩን ግጥም በግል ወይም በቡድን እንዲደግሙት ማበረታታት።
- ስለ መዝሙሩ መልዕክት እና ዜማ ምን እንደተሰማቸው እንዲናገሩ ማበረታታት።

## 2.4.ቀለል ባሉ ምቶች መወዛወዝ

**(ስርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-8)**

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ተማሪዎች ቀለል ባለ ምት ውዝዋዜን ይማራሉ።

❖ ምቶቹ ሲፈጥኑ እና ሲዘገዩ የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን ከምቱ ጋር ማዛመድ ይችላሉ፡፡

❖ አካላቸውን በማፍታታት የስሜት የአይምሮ እና የአካል መነቃቃት ያገኛሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

❖ የመለማመጃ ክፍል ወይም ክፍት ቦታ

❖ በአካባቢ የሚገኝ የምት መሳሪያ

❖ በድምጽ የተቀረጸ ቀላል ምት ያለበት ሙዚቃ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

❖ ቀላል ምት በከበሮ ወይም በሌላ የምት መሳሪያ በመምታት ተማሪዎች በምቱ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

ቀለል ያሉ ምቶችን መጠቀም ማለት ያልተወሳሰቡ የሙሉ ጊዜ ኖታ የግማሽ ኖታ አይነት ረዘም ያሉ ኖታዎችን መጠቀም ማለት ነው ፡፡ በጣም የተቆራረጡ እና ፈጣን ምት ያላቸውን ኖቶች በዚህ የክፍል ደረጃ ለልጆች መጫዎት ልጆችን ስለሚከብዳቸው በትምህርቱ ላይ ፍላጎት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡


## ቀላል ምቶችን የሚከተሉ የውዝዋዜ ጨዋታዎች

ተማሪዎቸ መጀመሪያ ከመወዛወዛቸው  በፊት ቀለል ያለ የምት ጨዋታ ማሳየትና ያዩትን ቀላል ምት ላይ ውዝዋዜ እንዲጨምሩ ማድረግ ፡፡

## ጨዋታ እና ወዝዋዜ- አንድ


ልጆች በተርታ ወይም ክብ ሰርተው እንዲቆሙ በማድረግ ሰማቸውን በየተራ በሶስት የምት ጊዜ በመክፈል እያጨበጨቡ እንዲናገሩ ማድረግ ፡፡ለምሳሌ የተማሪው ስም አበበ ቢሆን የስሙን ፊደሎች በሶስት ምት ዋጋ በመተካት ከስሙ መጨረሻ አንድ ምት ዋጋ እረፍት(Rest) በመጨመር ምቱ ዜማ እንዲኖረው በማድረግ ከጭብጨባ ጋር እንዲል ማድረግ  ተማሪው ስሙን ለሶስት ምት ከፍሎ ካለ በኋላ ሌሎቹ ተማሪዎች የእሱን ስም ደግመው እንዲሉ ማድረግ ወደ ሌላው ተማሪ ስም ከማለፋቸው በፊት፡፡

የተማሪው ስም አንጁሎ ቢሆን



አን ጁ ሎ


የተማሪዎቹ ስም በሶስት የድመጽ ምት ያልተመቸ ከሆነ የመሃሉን እሩብ ምት ወደ ሁለት የስምንተኛ ኖታ በመቀየር መጫወት ለምሳሌ፣ የተማሪዋ ስም አለሚቱ ቢሆን ..




**አ ለ ሚ ቱ**

## ጨዋታ እና ውዝዋዜ ሁለት

ከበሮ ወይም ሌላ የምት መሳሪያን በመጠቀም ቀለል ያሉ ምቶችን ከበሮ ላይ በመጫወት ልጆች አብረው ከምቱ ጋር እየተወዛወዙ እንዲከተሉ ማድረግ፣ምቱን በዝግታ ጀምሮ እንደ ሁኔታው ፈጠን በማድረግ ልጆች ከምቱ ጋር እንቅስቃሴያቸውን እንዲያስተካክሉ መርዳት



የምቶቹን አይነት በተለያየ ኖቶች በመተካት መጫወት



በውዝዋዜው ወቅት ተማሪዎች ከምቱ ጋር መላ ሰውነታቸውን እንዲያንቀሳቅሱ እጃቸውን ፣እግራቸውን፣ወገባቸውን በእንቅስቃሴው ውስጥ እንዲያካትቱ መርዳት፡፡

**ጨዋታ ሶስት**

ልጆች በማጨብጨብ፣ በእግራቸው ጣቶች ምት የሙዚቃ ምት እንደምንከተለው በመምታት፣ በጣቶች በመሃል እና በአውራ ጣት ቀጭ የሚል ድምጽ በመፍጠር መጨረሻ ላይ በመዝለል ቀለል ባለ ዜማ የሚጫወቱት ነው፡፡ ቃላቱን ከድርጊት ጋር እያዋሃዱ መጫወት ያስፈልጋል፡፡

//

**በሁለቱ እጆቼ ቸብ ቸብ ቸብ**

**በእግሮቼ ጣቶች ትም ትም ትም**

**በሁለቱ ጣቶቼ ቀጭ ቀጭ ቀጭ**

**በሁለቱ እግሮቼ እንጣጥ እንጣጥ እንጣጥ**

**እላለሁ እጫወታለሁ**

**እላለሁ እጫወታሁ**

**ከእንቅስቃሴ ጋር የተዛመዱ ቀላል መዝሙሮች ፡፡**

ምሳሌ ሸረሪት ቀስ በቀስ ወደ ላይ ወጣች ሲባል ልጆች እጆቻቸውን ወደላይ ቀስ በቀስ ከፍ ያደርጋሉ ንፋሱ ወደ ግራ ወደ ቀኝ አደረጋት በሚሉበት ጊዜ ደሞ ሰውነታቸውነ ወደ ግራ ወደ ቀኝ በማድረግ መዝሙሩን ከእንቅስቃሴ ጋር ያዛምዳሉ፡፡

## ሽረሪት ቀስ በቀስ ወደ ላይ ወጣች

ሽረሪት ቀስ በቀስ

ቀስ በቀስ ወደ ላይ ወጣች

ንፋሱ  መጥቶ ወደ ግራ

ወደ ቀኝ አደረጋት

ከታች የተመለከተውን መዝሙር ዜማ በአካባቢው የታወቀ ከሆነ ማዘመር ካልሆነ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በሚያውቁት መዝሙር መተካት

## ድንብሽ ለድንብሽ

ድንብሽ ለድንብሽ ድንብሽ ኖራ

ኖራ መስኮራ መስኮርኮርኪ

ኮርኪ ሰላሌ ስላሌንቦ

ሌንቦ ክፍሌ ሌንቦ

ክፍሌ ላንቃ

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ከሚሰሙት ምት ጋር ውዝዋዜውን እንዲያዛምዱ ቀድሞ ለተማሪዎች ማስረዳት ከመምህሩ(ሯ)ይጠበቃል፡፡

- ተማሪዎቸ በራሳቸው ምቶችን ፈጥረው ከምቱ ጋር የሚስማማ ውዝዋዜ እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡
- መምህሩ(ቷ) ቀለል ያለ ምት በአካበቢ በሚገኝ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫውቶ ማሳየት፡፡
- ልጆች በአካበቢያቸው ባለ የምት መሳሪያ ቀለል ያሉ ምቶችን እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የሰሙትን ምት ተከትለው እንዲወዛወዙ መርዳት፡፡
- ተማሪዎቸ በውዝዋዜው ወቅት እርስ በእርስ በመተያየት አንዱ የሌላውን እንዲያስመስል መምራት ከመምህሩ(ቷ )ይጠበቃል፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ተማሪዎች እንቅስቃሴዎቹን መተግበራቸውን መከታተል፡፡
- በራሳቸው የፈጠሯቸውን እንቅስቃሴዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡
- እንቅስቃሴዎቹን ከጓደኞቻቸው ጋር በትብብር መተግበራቸውን መከታተል፡፡
- ልጆች የተጫወቱትን የግል የምት ኖታ አይነት መዝግቦ መያዝ ፡፡

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በመቸክቸክ እጃቸውን እንዲያፍታቱ ተደርጓል፡፡ ቀለል ያሉ መስመሮችን እንዲሁም ቅርጾችን እንዲለዩ ተድርገዋል፡፡ ቀለል ያሉ ቅርጾችን የውስጥ አካል መቀባት ተለማምደዋል፡፡

ቀለል ያሉ ለህጻናት በሚሆኑ የሙዚቃ ምቶች እንዲወዛወዙ እንዲሁም ምቶቹን አካባቢ ላይ ባለ የምት መሳሪያ ደግመው እንዲጫወቱ ተደርጓል፡፡

ስለ ቤተሰብ የሚያወሱ መዝሙሮችን ተማሪዎች ዘምረዋል፡፡ስለ መዝሙሮቹ መልዕክት መረዳት ችለዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ትምህርቶች ተማሪ ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ አስተማሪው(ዋ) ተግብረዋል ተብሎ ይታሰባል ፡፡




## በቃል የሚመለስ መልመጃዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1.  ይሄ መስመር ምን መስመር ይባላል፡፡

   ሀ. አግድም ለ. ቀጥታ ሐ. ዚግዛግ


2. ከሚከተሉት ቅርጾች ውስጥ ሞላላ ቅርጽ የትኛው ነው፡፡

   ሀ.  ለ.  ሐ. 

3. ህጻን ልጅ ለማስተኛት የማባበያ መዝሙር የትኛው ነው

   ሀ. እሹሩሩሩ ለ.ወንድሜ ያዕቆብ ሐ.እንማር

4. ከነዚህ ቅርጾች ውስጥ ውስጡ የተቀባው የትኛው ነው

   ሀ.  ለ  ሐ. 

መልስ

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ
4. ለ

# ምዕራፍ -3
# ባህሎች

(ለምዕራፉ የተሰጠ -35 ክፍለ ጊዜ)

## መግቢያ

ባህል የአንድ ማህበረሰብ ልምዶችን እምነቶችን፣የአኗኗር ዘይቤዎችን እንዲሁም የተለያዩ የማህበረሰቡ ክንውኖቸን አቅፎ የሚይዝ ነው። ሁሉም ማህበረሰብ እንደሚኖርበት ቦታ እና አካባቢ የራሱ መገለጫ የሆነ የህይወት ልምምድ አለው። ከልምምዶቹ ውስጥ እምነት ፣የተለያየ ጥበብ እና ሙዚቃ፣ውዝዋዜ ፣አለባበስ ፣ ወግ ይካተታል።

በዚህ ምዕራፍ ልጆች የባህላቸው የውዝዋዜ ፣የመዝሙር ፣እንዲሁም የቀለም ሃብቶችን እንዲያውቁ ይጠበቃል። በአፈ ታሪኮች በወጎች ስለ ባህላቸው እንዲሁም ስለ አካባቢ በጎ ልምዶች እንዲቀስሙ ይደረጋል።

መምህሩ(ሯ) በምዕራፉ የቀረቡትን ተረቶች አፈታሪኮች ፣መዝሙሮች በቀጥታ በመውሰድ ወይም ከአካባቢው ጋር አዛምዶ ለልጆች በሚመጥን መልኩ መስጠት ይጠበቅበታል(ባታል)።

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የአካባቢውን ውዝወዜ ፣ሙዚቃ ያውቃሉ ።
- የተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎችን አለባበስ ይረዳሉ።

- ❖ የአካባቢያቸውን ውዝዋዜ አስመስለው ይጫወታሉ፡፡
- ❖ በአካባቢያቸው እንዲሁም በሃገራቸው ያሉ ተረቶችን እና እንቆቅልሾችን ይረዳሉ፡፡
- ❖ የአካባቢያቸውን ቀለማት እንዲሁም የሰንደቅ አላማ(ባንዲራ) ቀለሞች ይለያሉ፡፡
- ❖ መሰረታዊ  ቀለሞችን መለየት ይችላሉ ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ❖ የክልል እና የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ
- ❖ የአካባቢው የባህል አልባሳት
- ❖ የአካባቢውን ባህል የሚገልጹ ስዕሎች
- ❖ የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎች ቅጂ ካሴት
- ❖ የድምጽ እና የምስል ማጫወቻ (ቴሌቭዥን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ ወዘተ.....)
- ❖ በአካባቢ ሊገኙ የሚችሉ ቀለማትን የሚያሳዩ ምስሎች
- ❖ እርሳሶች ባለ ቀለም መጻፊያ ቁሶች..
- ❖ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያየ ቀለም ያላቸው ግብአቶች...

**ጠቃሚ መረጃ**

ልጆች የተለያዩ ባህሎችን እንዲገነዘቡ ጭፈራዎችን ሙዚቃዎችን ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ልጆች አስመስለው በሚጫወቱበት ጊዜ ትክክል ናችሁ አይደላችሁም ብሎ መዳኘት አያስፈልግም ፡፡

በራሳቸው የተሰማቸውን የተመለከቱትን እንዲጫወቱ ማበረታታት ይገባል፡፡

ቀለማትን በመጀመሪያ ከአካበቢያቸው እንዲለዩ ማድረግ ይገባል፡፡

**ቀለሞች በአካባቢ የምናገኝበት መንገድ**

ቀይ ቀለም(ከበርበሬ ፣ከቀይ ስር፣ከቀይ አፈር)

ቢጫ (ከእርድ፣በቢጫ አፈር)

አረንጓዴ(ከቅጠላ ቅጠል)

ሰማያዊ (ከካርቦን ወረቀት፣ጉሎ፣የዶቅማ ፍሬ)

ነጭ (ከቾክ ፣አመድ፣ የበቆሎ ዱቄት፣ኖራ ድንጋይ)

ጥቁር (ከጥላሸት፣ከከሰል፣ከጥቁር አፈር)

**የማስተማሪያ ዘዴዎች**

- ታሪክ/ተረት ነገራ
- የሚና ጨዋታ
- የተማሪዎች የግል ስራ
- የተማሪዎች የቡድን ስራ
- ሰርቶ የማሳየት ዘዴ
- የሚሰሩትን ስራ መምራት/መከታተል
- በመዝሙር ማስጠኛ (whole song methd or phrasal song method ) ማስጠናት

## 3.1.አካባቢ እና ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጥበቦች (መዝሙሮች፣ቀለሞች፣ውዝዋዜዎች፣ተረቶች፣አፈ-ታሪኮች ፣እንቆቅልሾች እና ትወናዎች..ወዘተ)

### 3.1.1 -ተረት እና እንቆቅልሽ እንዲሁም አፈ ታሪክ

**(ስርዐቱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-10)**

ተረት ማለት ታሪክ ነገራ ነው፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ቃላዊ በሆነ መልኩ ይተላለፋል፡፡ተረት በሃገራችን የአንድ ማህበረሰብን ወግ ልማድ እና ስነምግባራዊ ትምህርት ይዞ ትውልድን በመልካም የሚያንጽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

እንቆቅልሽ በጥያቄና መልስ ምክንያታዊነትን እና ድብቅ ሃሳቦችን በጨዋታ መልክ የምንማርበት ዜዴ ነው፡፡

አፈ ታሪክ ስለ አንድ ጀብደኛ ወይም የተለየ ገድል የሚተርክ ታሪክ ነው፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተረቶቹን መልዕክት ይረዳሉ፡፡
- የተለያዩ ቀለል ያሉ እንቆቅልሾችን መመለስ ይችላሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ግብዓቶች

- ❖ ልጆች በህብረት የሚሰሩበት በቂ ክፍት ቦታ ወይም ክፍል
- ❖ የተረት የእንቆቅልሽ  መጻህፍቶች

## ማነቃቂያ

- ❖ ልጆች የሚያውቁትን ተረት እንዲያወሩ ማበረታታት፡፡

## ጠቃሚ መረጃ

ተረቶችን ቀስ ብሎ ማንበብ እንዲሁም የልጆቹን የመከታተል ሁኔታ በየመሃሉ ማረጋገጥ፡፡ለተረት እንዲሁም ለእንቆቅሽ የሚሆን ጊዜ መምረጥ ፡፡ ልጆቹ ነቅተው ተረቱን ሊሰሙ የሚችሉት በምን ግዜ ነው ብሎ ሰዐት መምረጥ ይገባል፡፡

ስለ አፈታሪክ ታሪኩን መንገር እንጂ አፈ ታሪክ ምንድን ነው የሚለውን ለልጆች አሁን ባሉበት የክፍል ደረጃ መናገር ተገቢ አይሆንም፡፡

## የማስተማሪያ ዘዴ

- ❖ የተለያዩ ተረቶችን እንዲሁም እንቆቅልሾችን እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ❖ ልጆች ተረቶችን አድምጠው የተረቶችን መልዕክቶ እንዲረዱ ማስቻል

- ተረቶችን እንቆቅልሾችን በራሳቸው ከአካባቢያቸው እንዲፈልጉ መርዳት
- በተማሪዎች መማርያ መጽሃፍ ላይ ያለውን ተረት ተማሪዎች አንብበው በራሳቸው እንዲረዱ ማበረታታት

**ተረት**

**ቀበሮ እና አውራ ዶሮ**

አንድ ቀን አንድ ቀበሮ ምግብ ፍለጋ ወደ ሰዎች መኖሪያ መንደር መጣ፡፡በመንደሩ አንድ አውራ ዶሮ አንድ ድንጋይ ላይ ቆሞ ኩሉሉ .......እያለ ሲጮህ ቀበሮው ሰማና ወደ አውራ ዶሮ ቀረብ ብሎ

"ሰላም ላንተ ይሁን ወንድሜ አውራ ዶሮ እንደምን ዋልክ" አለው::

አውራ ዶሮውም

" የዶሮ አምላክ ይመስገንና ሰላም ነኝ" ሲል መለሰ፡፡

ቀበሮም ቀጠል አድርጎ

"ወንድሜ አውራ ዶሮ ከሩቅ ሆኜ ድምጽህን ስሰማ ደስ የሚል መሆኑን ተረዳሁ፡፡በእርግጥም ድምጽህ በጣም ደስ ይላል፡፡ ወደዚህም የመጣሁት ቀረብ ብዬ ብሰማው እንዴት ደስ እንደሚል ለማረጋገጥ ነውና ፣እስቲ እባክህ አንዴ ቀረብ በለኝና አሰማኝ" ሲል ለመነው::

አውራ ዶሮውም በቀበሮው ሙገሳ እጅግ በጣም ተደሰተ ወዲያውም ወደ ቀበሮው ቀረብ በማለት ጎንበስ ቀና አለና አይኑን ጨፍኖ ኩኩሉሉ…ኡኡ….ብሎ ሳይጨርስ ቀበሮውም ዘሎ የዶሮውን ክንፍ ጭምድዶ ይዞ ወደ ዋሻው ይዞት መሮጥ ጀመረ፡፡አረኞችም ቀበሮ ዶሮውን ይዞት ሲሮጥ አይተው ኖሮ ከኋላ እየተከተሉ ያሳድዱት ጀመር፡፡በዚህ ጊዜ አውራ ዶሮ አንድ መላ መጣለት፡፡

“ይህውልህ ወዳጄ ቀበሮ እረኞች ዶሯችንን ወሰደ እያሉ እየሮጡ ነው ፡፡ተከታትለው መጥተው እንዳይደበድቡህ ፡፡ የእናንተ ዶሮ አይደለም በላቸው” ሲል ዶሮው ቀበሮውን መከረው፡፡

ቀበሮውም እውነት መስሎት ወደ እረኞቹ ዞሮ፣

“እናንተ እረኞች ዶሮው የእናንተ አይደለም የኔ ነው” ሲል ፡፡ አውራ ዶሮውም ከቀበሮው አፍ አፈትልኮ በመሮጥ አንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ቁጭ አለ፡፡ ከዛም ዶሮው ቀበሮውን ቁልቁል እየተመለከተ

“ይሄውልህ ወዳጄ ቀበሮ በአለም ላይ አንተ ብቻ ብልጥ የሆንክ እንዳይመስልህ፡፡ ሰውን በብልጠት ማታለል የጥሩ ስነ ምግባር ስው ድርጊት አይደለም፡፡” ሲል ተናግሮት አመለጠ፡፡

## ተረት

## አንድ ሽማግሌ እና ነብር

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ትልቅ ሽማግሌ መንገድ ሲሄዱ አንድ አዳኞች የሚያባርሩት ነብር ከመንገዳቸው መጣ፡፡

“እባኮት አባባ አዳኞች ሊደበድቡኝ እየተከተሉኝ ነው አድኑኝ “አላቸው፡፡

ሽማግሌውም ነብሩ ስላሳዘናቸው በያዙት ማዳበሪያ ውስጥ ከተው ደበቁት፡፡ ነብሩን የሚፈልጉ አዳኞችም ሽማግሌው ጋር ደረሱ እና

“አባባ አንድ ነብር በዚህ ሲሄድ አይተህዋል?” ሲሉ ጠየቋቸው ፡፡

ሽማግሌውም ሰውዬ

“እኔ መንገዴ ላይ ምንም ነብር አላየሁም” ሲሉ ነገሯቸው፡፡አዳኞቹም ወደ ሌላ መንገድ ነብሩ ሄዷል በቃ ብለው እየሮጡ በሌላ መንገድ ሄዱ፡፡

መነኩሴውም አዳኞቹ መሄዳቸውን አይተው ማዳበሪያቸውን ፈተው

“አያ ነብር በል ሊደበድቡህ የነበሩት ሰዎች ሄደዋል በል ውጣ” አሉት፡፡

ነብሩም

“ እንዴት በዚህ ማዳበሪያ አስረው ካስራቡኝ በኋላ ወዴት ነው የምሄደው ባይሆን እርሶ የሚበላ ነገር አምጥተው ቶሎ ይመግቡኝ ወይም እቤቶ ተሸክመው ይውሰዱኝ” ሲል መለሰላቸው፡፡

“እኔ ከሚደበድቡህ ሰዎች ባስጣልኩህ እንዴት እኔን የሚበላ አምጣ ብለህ ታስቸግረኛለህ?” ብለው....” በል ወደ ሌሎች እንስሶች ጋር ለፍርድ እንቅረብ እና እንስሶች ይፍረዱኝ” ሲሉ ነገሩት፡፡

ከዛ ም ሽማግሌውና ነብሩ ወደ እንስሶች ፍርድ ቤት (ሸንጎ)ሄደው ጉዳያቸውን ያስረዱ ጀመር፡፡

መጀመሪያ ዝንጀሮ ለፍርድ ተነሳና

“እንዴት በማዳበሪያ ይዘው ካቆዩት በኋላ ያለ ምግብ ነብሩን ሂድ ይሉታል?” ብሎ ለነብሩ አግዞ ፈረደ፡፡

ፍየልም ተነሳና ሽማግሌውን

“በሉ ነብሩን ተሸክመው እቤቶ ወስደው ሊያበሉት ሊያጠጡት ይገባል” ሲል ፈረደ፡፡ውሻም ጅብም ለነብሩ አግዘው ፈረዱ፡፡

በመጨረሻም ጦጢት ትፍረድ ተባለ እና ጦጢት መጥታ ነገሩን አየች፡፡ ነብርም

"እኝህ ሽማግሌ በርሃብ ማዳበሪያ ውስጥ ካስቀመጡኝ በኋላ ያለምንም ምግብ ሂድ አሉኝ “ሲል ለጦጢት ነገራት፡፡

ጦጢትም "እኔ መሬት ላይ ሆኜ መፍረድ አልችልም ዛፍ ላይ ወጥቼ ልፍረድ" ስትል ተናገረች፡፡ነብሩ እና ሽማግሌውም እሺ ዛፍ ላይ ወጥተሽ ፍረጂን አሏት፡፡

ጦጢትም ዛፍ ላይ ከወጣች በኋላ

"አባት እርሶ በጣም ደካማ ኖት ነብር ደሞ በጣም ጉልበተኛ ነው፡፡እና እኔ ነብሩን ከአዳኞች አዳንኩት ያሉትን ነገር አላመንኩበትም እስቲ አሳዩኝ እንዴት አድርገው ነው ትልቁን ነብር ከአዳኞች ያዳኑት ?"ብላ ጠየቀቻቸው፡፡

ሽማግሌውም ነብሩን ወደ ማዳበሪያቸው ካስገቡ በኋላ ቀና ብለው ጦጢትን ቢያዩ የማዳበሪያውን አፍ በገመድ እንዲያስሩት ነገረቻቸው፡፡ሽማግሌውም ማዳበሪያውን አሰሩት ፡፡ጦጢትም

"አባት እርሶ እሱን ቢያድኑትም ነብሩ ግን እርሶን ተሸክመው ወስደው ምግብ አብሉኝ ማለቱ ስህተት ነው፡፡ስለዚህ እርሶ አሁን ይሂዱ "ብላ ፈረደች፡፡ ነብሩም ከማዳበሪያው ውስጥ መውጣት ስላልቻለ፡፡እያለቀሰ መጮህ ጀመረ ፡፡

"በቃ አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርጉልኝ" እያለ ማዳበሪያ ውስጥ መወራጨት ጀመረ፡፡ ሽማግሌውም በል ከዚህ በኋላ እንደዚህ ነገር እንዳታደርግ ለአሁኑ ይቅርታ አድርጌልሃለሁ ብለው ከማዳበሪያ አወጡት፡፡ ነብሩም በሰራው ስራ ተጸጽቶ" ይቅርታ ስላደረጋችሁልኝ አመሰግናለሁ "አለ፡፡ ሽማግሌውም ነብሩም በሰላም ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

## አንበሳ እና አይጥ

አንድ ወቅት የእንስሶች ንጉስ የነበረ አንድ አንበሳ በጫካ ውስጥ ይኖር ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ይህ አንበሳ ምግቡን ፍለጋ ከጫካ ውስጥ ሲዘዋወር አንዲት አይጥ አገኘ፡፡ አይጧንም አግኝቶ ሊበላት ሲል አያ አንበሳ እባክህ አትብላኝ አለችው፡፡አያ አንበሳም ዛሬ እርቦኛል አንቺን ካልበላሁ ታዲያ ምን ልብላ ሲል ተናገረ፡፡

አይጧም የዛሬን ማረኝ እንጂ አንድ ቀን ውለታህን እመልሳለሁ አለችው፡፡ አንቺ በአካልሽ ትንሽ ነሽ እንዴት ለእኔ ውለታ ትመልሻለሽ አላት፡፡ የዛሬን ማረኝ እንጂ አንድ ቀን ውለታህን እመልሳለሁ አለች፡፡

አንበሳው እየሳቀ በይ ለዛሬ ሂጂ ብሎ አዘነላትና ለቀቃት፡፡አይጧም እየሮጠች ከፊቱ ሄደች፡፡ አንበሳውም የወደቀ ስጋ አገኘና በልቶ ረሃቡን አስታገሰ፡፡

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አንበሳው የሚበላ ስጋ ፍለጋ በጫካው ውስጥ ሲዘዋወር ድንገት አዳኞች የአዘጋጁት የገመድ ወጥመድ ውስጥ ገባ ፡፡

አንበሳው ቢታገል ቢታገል ገመዱን መፍታት አልቻለም፡፡ ያን እለት አይጥ በአጋጣሚ መንገድ ስታልፍ አንበሳ ታስሮ አየች፡፡ ወደ አንበሳውም በመቅረብ አያ አንበሳ አሁን ገመዱን ቆርጬ ከገባህበት ገመድ አስወጣሃለሁ፡፡

የአይጥ ጥርስ ጠንካራ እና ብዙ ነገር መቁረጥ የሚችል ስለሆነ አይጧ ገመዱን በፍጥነት ቆርጣ ጣለችው፡፡አንበሳውም ነጻ ወጣ ፡፡ አንበሳውም ውለታህን እመልሳለሁ ያለችውን አስታውሶ በጣም ተገረመ፡፡አይጧን አመስግኗት በሰላም ወደ ቤቱ ሄደ፡፡

**መምህሩ(ሯ) ተረቱ ሲያልቅ ተማሪዎች ስለ ተረቱ ምን እንደተሰማቸው እንዲሁም ምን እንደተረዱ/እንደተማሩ መጠየቅ ፡፡**

**በዚህ ተረት ውስጥ ልጆች መልካም ፍርድ መስጠት ጥሩ እንደሆነ ይማራሉ፡፡ጥፋተኛም ይቅር በሉኝ ካለ ለጥፋት ይቅርታ መባባል እንደሚገባም ያስተምራል፡፡**

**እንቆቅልሽ ጨዋታ**

እንቆቅልሽ ልጆች ብዙ ጊዜ ለሁለት በመሆን የሚያደርጉት የጥያቄና መልስ ጨዋታ ነው ፡፡ ጠያቂ ጥያቄውን ከመጀመሩ በፊት

“እንቆቅልሽ” ይላል፡፡

“ “ምን አውቅልህ(ሽ)፡፡ በማለት ይመልሳል፡፡በመቀጠል ጠያቂ ጥያቄውን ይጠይቃል፡፡ተጠያቂው መልሱን ካወቀ መልሱን ይናገራል፡፡ተጠያቂው የጥያቄውን መልስ ካላወቀ፡፡”አላውቀውም “በማለት ይመልሳል፡፡በዚህ ጊዜ ጠያቂ

“ሃገር ስጠኝ “ይላል

ተጠያቂም በሃገራችን የሚገኝ አንዱን የአካባቢ ስም ይጠራል፡፡ ጠያቂም

ተጠያቂው የሰጠውን ሃገር በመጥራት

“ጂንካ ሄጄ ምን አጥቼ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ ሲጠማኝ ቡና ጠጥቼ ገንፎ በልቼ” ብሎ ካለ በኂላ

መልሱን ይናገራል፡፡

## የእንቆቅልሽ ጨዋታዎች

| | |
|---|---|
| ትልቁ አዞ ተጠማዞ | መልስ -መንገድ |
| አራት እግር አለው ወንዝ የማይሻገር | መልስ - አልጋ |
| ከቁርስ በፊት የማይበላ | መልስ- ምሳና ፣አራት |
| ጸጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ | መልስ - ሱፍ |
| ከመብላታችን በፊት የምንሰብረው | መልስ - እንቁላል |
| እናትየው ጥቁር ለጆቿ ነጫጭ | መልስ -ጀበና እና ሲኒ |
| ገላዬ ብርቱካናማ ኮፍያዬ አረንጓዴ እኔ ማን ነኝ | መልስ- ካሮት |
| ወጣት ሳለሁ እረዝማለሁ ሳረጅ አጥራለሁ እኔ ማን ነኝ | መልስ -ሻማ |

| | |
|---|---|
| በራሴ አፍ የለኝም ግን ሰዎ የተናገሩትን እደግማለሁ | መልስ -የገደል ማሚቱ |
| ታቹ በድን እላዩ በድን መሃሉ ነፍስ አድን | መልስ -አክንባሎ ፣ምጣድ እና እንጀራ |
| ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ሲቆሽሽ | መልስ- አይን |
| የሚነጣ ሲጸዳ የሚጠቁር | መልስ-ብላክ ቦርድ(ጥቁር ሰሌዳ) |

አፈ ታሪክ

ስለ አለም እና ምድራችን ላይ ስላሉ ሚስጥራዊ አፈጣጠሮች መላምት የሚያስቀምጥ ቃላዊ ትውፊት ነው፡፡

Legend የሚለውንም አፈ ታሪክ ተብሎ ልናገኘው እንችላለን፡፡ ሌጀንድ የምንለው ስለ ግለሰቦች የጀብዶ ታሪክ የሚያወሩ ቃላዊ ትውፊቶችን ነው፡፡

ለምሳሌ

አፈታሪክ (myth)- ለምን ሰማይ እሩቅ ሆነ? ለሚለው ጥያቄ "አንዲት በቅሎ ረግጣው ነው እንጂ በጥንት ሰማይ እሩቅ አልነበረም፡፡" ተብሎ መልስ ሲመለስ የምንሰማው አይነት ፡፡የተላያዩ የፍጥረታትን የአፈጣጠር ሚስጥር በመላምት የምናስቀምጥበት ነው፡፡

## አፈታሪክ (myth)

## የሙቁምሳ ታሪክ

በኦሞ ወንዝ ዳርቻ በጥንት ጊዜ  የሚኖር ሙቁምሳ የሚባል ሰው ነበረ፡፡ሙቁምሳ በጣም ግዙፍ እና በጣም ብዙ ጉልበት ያለው ሰው ነበር ፡፡ ሙቁምሳ በጣም ረዥም ስለሆን ሰዎች ከእሱ ስር ጉልበቱ ጋር አይደርሱም ነበር፡፡

ሙቁምሳ መንገድ ሲሄድ የጸሃይ ብርሃን ካስቸገረው ድንገት አንዱን ትልቅ ዛፍ ጎትቶ ለራሱ ጥላ ያደርግ ነበር ፡፡ ሙቁምሳ ጥላ ሊያደርጋቸው የጎተታቸው ዛፎች በዚህ ዘመን ተንጋደው ቀርተው ይታያሉ፡፡

ሙቁምሳ ገበጣ ይጫወት ነበር፡፡ የገበጣውንም ቀዳዳ በድንጋይ ላይ ያለምንም መቆፈሪያ በእጆቹ ነበር የሚያጎደጉደው፡፡

ሙቁምሳ አካባቢው ላይ የተለያዩ ቋጥኞችን በእጁ በመፍለጥ አካባቢው ለሰዎች ምቹ እንዲሆን ያደርግ ነበር፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- መምህሩ የተማሪዎችን በትክክል ተረቶቹንና አፈታሪኮችን መከታተላቸወን ይመለከታል
- ልጆች ስለ ተማሩት መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ
- ስለ ተረቶቹ መለዕክት በቡድን ተወያይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ

❖ ስለ ተረቶቹ እና ስለ አፈታሪኮቹ ገጸ ባህሪያት እንዲሁም መልዕክት በተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ላያ ያሉትን የቃል ጥያቄዎች መጠየቅ፡፡

### 3.1.2. ውዝዋዜ

(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-10)

**መግቢያ**

በሃገራችን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች እንደመኖራቸው ሁሉም ብሄሮች የተለያየ አይነት ውዝዋዜ አላቸው፡፡

ጭፈራዎቹም በእግር ፣በእጅ፣በትከሻ እና በዳሌ እንደ አይነቶቹ ይተገበራሉ፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

❖ ቀለል ያሉ የአካባቢያቸውን እና የሃገራቸውን ውዝዋዜ መጫዎት ይቻላሉ

❖ ውዝዋዜዎቹን በቡድን ይለማመዳሉ

❖ ምትን ከእንቅስቃሴ ጋር ለማዋሃድ ይሞክራሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

❖ ለአካባቢያችው ውዝዋዜ የሚረዳ በድምጽ የተቀዳ ዘፈን

❖ የምስል እና የድምጽ ማጫዎቻ መሳሪያ

❖ ለውዝዋዜ የሚሆን ባህላዊ አላባሳት

## ማነቃቂያ

- በቴሌቭዥን ወይም በሌላ መንገድ ከዚህ በፊት የተመለከቷቸውን ውዝዋዜዎች እንዲናገሩ ማድረግ ።ተማሪዎች የሚያውቁትን ባህላዊ ውዝዋዜ እንዲወዛወዙ ማድረግ።

## ጠቃሚ መረጃ

መምህሩ በአካባቢያቸው ያሉ ጭፈራዎችን በምስል ወይም እራሱ ከቻለ በመንቀሳቀስ  ወይም ሌላ ተወዛዋዥ ጋብዞ ሊያሳይ እና የውዝዋዜዎቹ አይነት  በተለየ የትኛውን የሰውነት ክፍል እንደሚጠቀሙ ማብራራት ይገባዋል።

የባህል ውዝቃዜዎች ለህጻናት የማይሆኑትን መምረጥ ያስፈልጋል ።ከበድ ያሉ የውዝዋዜ አይነቶችን በመተው ቀለል ያሉትን ውዝዋዜዎ እንዲጫወቱ ማድረግ ከመምህሩ(ሯ)ይጠበቃል።



ምስል.3.1 .የጋሞ ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል 3.2 የኛንጋቶም ማህበረሰብ ባህላዎ ጭፈራ



ምስል 3.3 የደራሼ ማህበረሰብ ባህላዎ ጭፈራ



ምስል.3.4

የጉራጌ ባህላዊ ጭፈራ

ከአካባቢያችን ካሉ ጭፈራዎች በመቀጠል በሃገራችን የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችንም ጭፈራ ማሳየት ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡



**ምስል**.3.5 በቅደም ተከተል የአማራ ፣የኦሮሞ፣የሱማሌ ጭፈራዎች

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ባህላዊ ጨዋታዎችን በምስል ወይም ሰርቶ በማሳየት እንዲመለከቱ ማድረግ
- ልጆች በግል እንዲሁም በቡድን የተለያዩ ውዝዋዜዎችን እንዲለማመዱ ማድረግ
- የባህል ውዝዋዜ ከባህል አልባሳት ጋር ያለውን ግንኙነት መግለጽ፡፡
- በየተራ ውዝዋዜያቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡
- በተማሪዎቸ መማሪያ ላይ ያሉ ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ጭፈራዎቹ ያሏቸውን ሃሳቦች የሚገልጹባቸውን ጥያቄዎች ላይ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ልጆች በግል እና በቡድን ሲወዛወዙ በጥሞና መመልከት
- ልጆች ስለ ውዝዋዜዎቹ የተሰማቸውን እንዲገልጹ ማድረግ
- ስለ ባህላዊ ጭፈራዎቹ ስለ አልባሳቶቹ ስለሴት እና ወንድ ጭፈራ ልዩነት በቃል መጠየቅ
- በተማሪ መማሪያ መጽሃፍት ላይ ያሉ የቃል ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲመልሱ ማበረታታት፡፡

### 3.1.3. መዝሙሮች

(ስርዐቱ የተሰጠ  ክፍለ ጊዜ-5)

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ❖ ስለ አካባቢያቸው የሚያወሱ መዝሙሮችን መዘመር ይችላሉ
- ❖ የመዝሙሮቹን መልዕክት ይረዳሉ

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ❖ ስለ ባህል እና ስለ አካባቢ የሚያስተምሩ መዝሙሮችን የያዙ የድምጽ ቅጅዎች
- ❖ መዝሙሮቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ የምት መሳሪያዎች(ከበሮ፣አታሞ፣ቃጭል)

**ማነቃቂያ**

- ❖ አካባቢያቸው ላይ ተወዳጅ የሆነ መዝሙር/ዘፈን እንዲጫወቱ ማበረታታት

**ጠቃሚ መረጃ**

- ❖ ልጆች በቡድን እና በግል ሲለማመዱ ምናልባት መዝሙሩን ቶሎ ካልቻሉት ልጆቹ እስኪችሉት ደጋግሞ ማሰማት እና አብሮ መዘመር ይገባል፡፡
- ❖ መዝሙሮቹ አጭር እና ቀላል ምትን የያዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ❖ ተማሪዎች የመዝሙሩን ግጥሞች መጀመሪያ ሀረግ በሃረግ እንዲያጠኑ ማድረግ፡፡
- ❖ ለብቻ እና በቡድን ዜማዎቹን ማለማመድ፡፡
- ❖ የመዝሙሮቹን የድምጽ ቅጅ ደጋግሞ እንዲሰሙት ማድረግ፡፡ቅጅው ከሌለ መምህሩ ደጋግሞ መዝሙሮቹን ለተማሪዎች ዘምሮ(ራ) ማሳየት፡፡

### ዝናብ ሂድልኝ

ዝናብ ሂድልኝ ነገ ተመለስልኝ
ዝናብ ሂድልኝ ዛሬ ጨዋታ አለብኝ

**ዝናብ ሂድልኝ**



## ልጅ ለመፈለግ መጥተናል ዛሬ በማለዳ

ልጅ ለመፈለግ  መጥተናል ዛሬ በማለዳ

ማንን ትፈልጋላችሁ ዛሬ በማለዳ

ሚሚን እንፈልጋታለን ዛሬ በማለዳ

እሷን መጥቶ የሚወስዳት ማን ጎበዝ አላችሁ

እሷን መጥቶ የሚወስዳት አቡሻ አለና

የኛ ልጅ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ

የኛ ልጅ በርታ በርታ እንዳትረታ

### ክትትል እና ግምገማ

- ❖ ሁሉም ተማሪ በመዝሙሩ መሳተፉን መከታተል እና መመልከት
- ❖ ተማሪዎቹ ስለ መዝሙሮቹ መልዕክቶች ሀሳባቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
- ❖ የተማሪዎችን የተሳትፎ መጠን መዝግቦ መያዝ፡፡
- ❖ ስለ መዝሙሩ ግጥም የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡

## 3.2. በአካባቢያችን ያሉ ቀለሞች

(ለርዕሱ የተሰጠ  ክፍለ ጊዜ-10)

### መግቢያ

አካባቢያችን በተለያየ ቀለም የተሞላ ነው፡፡ አልባሳታችን የቤቶቻችን ማስዋቢያዎች እንደምንኖርበት አካባቢ የተለያዩ ቀለማትን እንጠቀማለን፡፡እኛ አካባቢ ላይ አዘውትረን የምናየው ቀለም ሌላ ቦታ አዘውትረን ላንመለከተው

እንችላለን፡፡እንደምንኖርበት ቦታ የቀለም ምርጫችንም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ❖ በአካባቢያቸው ያሉ ቀለሞችን ይለያሉ
- ❖ በአካባቢያቸው ባሉ የቀለም ግብአቶች ሰንደቅ አላማ እንዲሁም የተለያዩ መለያዎችን ቀለም ይለያሉ እንዲሁም ማቅለም ይችላሉ
- ❖ ልብሶችን እንዲሁም የተለያዩ በክፍላቸው ያሉ ቁሳቁሶችን ቀለም ይለያሉ

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ❖ በአካባቢ የሚገኝ መጻፊያ እርሳስ ወይም ማቅለሚያ የሚሆን ግብአቶች
  (በርበሬ፣ከሰል፣ቾክ፣እርድ፣አፈር፣ቅጠላ ቅጠል)
- ❖ ለመሳል መተግበሪያ ወረቀት ወይም የመሳያ ሰሌዳ
- ❖ የሃገር ሰንደቅ አላማ እንዲሁም የክልሎች ሰንደቅአላማ

**ማነቃቂያ**

- ❖ አጠገባቸው ያለውን የጓደኛቸውን ልብስ ቀለም እንዲናገሩ ማበረታታት

**ጠቃሚ መረጃ**

ቀለሞች ልብሶቻቸውን ሊያበላሹባቸው ስለሚችሉ ልጆች ቀለም በሚያቀልሙበት ወቅት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መናገር ከመምህሩ(ቷ) ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም መጽሃፍቶቹ ላይ ቀለም እንዳይቀቡ ማስገንዘብ ፡፡ ተማሪዎች በተማሪዎች መማሪያ መጽፍ ላይ የተሰጧቸውን የሚያቀልሟቸውን ምስሎች በሌላ ወረቀት ለተማሪዎቹ ኮፒ በማድረግ ልጆች ኮፒ የተደረገው ላይ እንዲለማመዱ ማድረግ ከመምህሩ(ቷ) ይጠበቃል፡፡

በሚያቀልሙበት ወይም ባንዲራዎችን እና ቀለማት በሚያስቀምጡበት ወቅት ሲሳሳቱ በማበረታታት እንዲቀይሩ ማድረግ፡፡

**ቀለም ምንድን ነው**


አለማችን በልዩ ልዩ ቀለማት የተሞላች ነች፡፡በአካባቢያችን የምናያቸው ነገሮች በሙሉ የራሳቸው ቀለም እና መልክ አላቸው፡፡ ተራራው፣አበባው፣አትክልቱ፣ደኑ፣እንስሳው ፣አእዋፉ በሙሉ የራሱ ቀለም አለው፡፡ በአይናችን የምናያቸው ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ፍጥረት ሁሉ በራሱ የተለያየ ቀለም ያጌጠ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ቀለም በራሱ ቀለም ሆኖ እንዲታይ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጉታል፡፡ እነዚህም ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ የብረሃን ምንጭ፣ዓይናችን እንዲሁም ብርሃን የሚያርፍባቸው አከላቶችወይም ቁሶች ናቸው፡፡

አነስተኛ ብርሃን ባለበት ቦታ የደበዘዘ ቀለም ያለው መልክ ይታያል፡፡ሃይለኛ ብርሃን ባለበት ቦታ ደሞ ቀለሙ ጎልቶ እና ደምቆ ይታያል፡፡ የቀለም አይነቶችን በተለያየ ክፍል እንመድባቸዋለን፡፡በዚህም በመጀመሪያ ደረጃ መስራች ቀለማት የሚባሉ ቀለማት አሉ፡፡ እነሱም ቀይ ፣ቢጫ እና ሰማያዊ ቀለማት ናቸው፡፡

እነዚህ ሶስት ቀለሞች በመጀመሪያ ደረጃ መስራች ቀለማት ልንላቸው የቻልንበት ምክንያት ሶስቱን በመቀላቀል ሌሎቹን የተለያዩ ቀለሞች መፍጠር ስለሚያስችለን ነው፡፡

**ቀይ ቀለም** **ቢጫ ቀለም** **ሰማያዊ**



**የአልባሳት ቀለማት**



**ዱንጉዛ**

## ሰንደቅ ዓላማዎች



የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰንደቅ ዓላማ



የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ ሰንደቅ

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ልጆች የለበሷቸውን ልብሶች ቀለም ምን ምን አይነት ቀለም እንደሆነ ገለጻ ማድረግ፡፡
- ሰንደቅ አላመዎችን በማሳየት ስለ ቀለሞቹ ገለጻ ማድረግ፡፡
- ቀለሞች በመቀቢያ ቁሶቹ እንዴት እንደሚቀቡ ማሳየት፡፡
- አካባቢያቸው ዙሪያ ላይ ያሉ ቀለሞችን ከክፍል ውጪ ተማሪዎቹን በማስወጣት ማሳየት፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ተማሪዎች ቀለማትን መረዳታቸውን መከታተል ፡፡
- ስለ ሰንደቅ አላማ እንዲሁም ስለ ተማሪዎች ስለ አልባሶቶቻቸው ቀለማት እንዲገልጹ ማድረግ እንዲሁም ቀለማትን ሲቀቡ መመልከት
- ከክፍላቸው ውጪ ስለተመለከቱት ቀለማት በግል እንዲሁም በቡድን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
- የተለያዩ አልባሳትን እንዲሁም ምስሎችን በማየት ቀለሙን እንዲጠሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ቀለማትን ፣ውዝዋዜወችን እንዲሁም መዝሙሮችን የአካባቢን ብሎም የሃገርን ገጽታ በሚያሳዩ መልኩ ተምረዋል፡፡

ተረቶች ፣አፈታሪኮች፣ እና እንቆቅልሾችን ተማሪዎች እንዲተገብሩ በማድረግ ባህላቸውን እንዲሁም ትውፊታቸውን ከማወቅ በዘለለ ተረቶቹ እና አፈታሪኮቹ የያዙትን መልካም መልዕክት እንዲገነዘቡ ተደርገዋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ እንደ ዋና ተግባራት ተደርገው የተወሰዱት የምዕራፉ ወሰኖች

1. የተለያዩ ባህሎች ውዝዋዜ መተዋወቅ እንዲሁም መወዛወዝ
2. የተለያዩ አልባሳት ቀለሞችን መገንዘብ
3. መዝሙሮችን መተግበር
4. ተረት እና አፈ ታሪኮችን ማዳመጥ ፣እንዲሁም መረዳት

ተማሪዎቹን በአማከለ የትምህርት አተገባበር ተማሪዎች በቂ እውቀት በማግኘት የእንቅስቃሴዎቹን ተግባራትም ተግብረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

**የቃል መልመጃ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ።**

1. የባህልአለባሳት የአንድን አካባቢ ባህል መግለጽ ይችላሉ።
2. በሃገራችን የተለያዩ  የውዝዋዜዎች አይነቶች አሉ።
3. ተረቶች መልካም ስነምግባርን ማስተላለፍ ይችላሉ።
4. የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አንድ አይነት ቀለም ብቻ ነው ያለው።

**መልስ**

1. እውነት   2. እውነት   3. እውነት   4. ሐሰት

# ምዕራፍ -4
## ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማድነቅ

(ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ -35)

### መግቢያ

አንድን ባህል ማድነቅ ለባህሉ እውቅና መስጠት ነው፡፡አንድ ባህል በራሱ የተለየ እሴቶች አሉት ፡፡በሃገራችን በኢትዮጵያም የተለያዩ ባህሎች አሉን፡፡ በባህሎቻችን ውስጥ በጣም ብዙ ጠቃሚ እሴቶች ይገኛሉ፡፡

አንድን ባህል ማድነቅ ማለት ባህሉን ጠቃሚ ጎኑን ለመማር ፣ ለመልመድ ወይም ለመተግበር ፈቃደኛ መሆንንም ያካትታል ፡፡

የባህልም መገለጫው ብዙ ነው፡፡ ቋንቋው ፣አለባበሱ፣ አመጋገቡ፣ወጉ ፣ልምዱ በጥቂቱ እነዚህን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ባህል ማለት የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ እና እውቀት በመሆኑ የተለያዩ ባህሎችን በጎ ባህል ማወቅ አንድ አዲስ እውቀት እንደማግኛ ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተለያዩ ባህሎችን ይተዋወቃሉ መልካምነታቸውን ይገነዘባሉ
- በአካባቢያቸው ስላለው ባህላዊ ተግባራት በጥቂቱ ውዝዋዜን ፣ሙዚቃን፣ይገነዘባሉ
- ባህላዊ የሆኑ መዝሙሮችን ይዘምራሉ

- በምስሎች የተለያዩ ባህሎችን የቤት አሰራር ፣አልባሳት፣ ጌጣጌጦችን  መለየት ይችላሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ለሚና መጫወት(ለትወና የሚያገለግሉ ባህላዊ አልባሳት)
- የድምጽ እና የምስል መጫዎቻ
- የተለያዩ ስለ ባህል የሚገልጹ ምስሎች

**ጠቃሚ መረጃ**

በአካባቢያችን የተለያዩ ባህሎች እንደመኖራቸው መምህሩ(ሯ) በመምሪያው መሰረት የሚሆኑ የባህል ክንውኖችን ለሚና መጫወት ግብአት የሚሆኑ ሀሳቦችን እንዲያፈልቅ ይጠበቃል፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች**

- የሚና ጨዋታ
- የተማሪዎች የግል ስራ
- የተማሪዎች የቡድን ስራ
- ሰርቶ የማሳየት ዘዴ
- ተግባራዊ ስራ ማሰራት
- የሚሰሩትን ስራ መምራት/መከታተል
- በመዝሙር ማስጠኛ  (whole song methd or phrasal song method ) ማስጠናት

## 4.1.የቤተሰብ መዝሙሮች ፣ውዝዋዜዎች ፣ሚና መጫዎት እና ምስል

**(ስርአቱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-5)**

### 4.1.1.ስለ ባህል የሚናገሩ መዝሙሮች

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ስለ ባህል የሚያወሱ መዝሙሮችን ያውቃሉ፡፡
- መዝሙሮችን ስለምናጅብባቸው ባህላዊ መሳሪያዎች ይረዳሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- መዝሙሮችን የሚያሳዩ የድምጽ ወይም የምስል ማጫዎቻዎች
- በአካባቢ የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፡፡

**ማነቃቂያ ጥያቄ**


- ስለሚያውቋቸው የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲናገሩ ማበረታታት

**ጠቃሚ መረጃ**

ልጆች ስለአካባቢያችው ስላለ ባህል እንዲሁም ትውፊት በመዝሙር እንዲጫወቱ ማድረግ ይገባል፡፡በመዝሙሮቹ ውስጥ የባህል ውጤቶች መደነቅ እና መገለጽ አለባቸው፡፡

ስለ ሀገራችን የባህል መሳሪያዎች የሚናገር መዝሙር/ዘፈን ከመጫወታችን በፊት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በጥቂቱ እንመልከት፡፡

**የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች**



ምስል.4.1

ክራር ባለ ስድስት ወይም ባለ አምስት ክር የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል.4.2

ከበሮ የኢትዮጵያ የምት ሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል.4.3

ማሲንቆ ባለ አንድ አውታር የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል.4.4

በገና ባለ አስር አውታር የሙዚቃ መሳሪያ ፡፡በገና በይበልጥ ለሀይማኖታዊ አገልግሎት የሚውል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



ምስል.4.5.

ዋሽንት የሃገራችን ባህላዊ የትንፋሽ መሳሪያ



ምስል.4.6. ፊላ

እነዚህ ስድስቱን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጠቀስን እንጅ በሃገራችን የተለያዩ የትንፋሽ ፣የምት፣የክር መሳሪያዎች አሉ፡፡

## ስለ ባህላዊ መሳሪያዎቻችን የምናወሳበት መዝሙር

### እኛም አለን ሙዚቃ

እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ

እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ

ከበሮችን

ቡም ቡም ቡም ቡም

ክራራችን

ታታታታ

ማሲንቋን

ላላ ላላ

በገናችን

ቦም ቦም ቦም ቦም

## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- መዝሙሮቹን በመጀመሪያ ተግብሮ ማሰማት፡፡
- የመዝሙሮቹን ግጥም በመዝሙር ማስጠኛ ዘዴዎች በአንዱ እንደ አስፈላጊነቱ ማስጠናት፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያ ምስሎችን ማሳየት፡፡

## 4.1.2.ሚና መጫዎት

**ከርዕስ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የተለያዩ ባህሎችን ይተዋወቃሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ስላለው ባህላዊ ተግባራት በሚና ጨዋታ ይረዳሉ፡፡

**ማነቃቂያ**

- የሚያውቁትን ድራማ ወይም ተወኔት ካለ እንዲናገሩ ማድረግ ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ለሚና ጨዋታ የሚሆን ክፍት ቦታ ወይም ክፍል
- ለሚና መጫወት(ለትወና የሚያገለግሉ ባህላዊ አልባሳት)

**ጠቃሚ መረጃ**

የእርቅ ስርዓቶቸን፣የሰርግ ስርዓቶችን፣የስራ ባህላዊ ተግባራትን መርጦ ልጆች በቡድን ስለ ባህሉ ሚና ተሰጥቷቸው እንዲጫወቱ ከማድረጋችን በፊት በደንብ የባህሉን ስርዐት እንዲያውቁት

ማድረግ ይገባል፡፡

## የሚና ጨዋታ ምሳሌ .1 (የጋሞ ባህል የእርቅ ስርዐት)



ምስል.4.7

ሁለት ጎረቤቶች በግጦሽ መሬት ስላልተስማሙ የሚካሄድ እርቅ፡፡ በዳይ(ጥፋተኛው ሰው) ከብቶቹ የተበዳይን የማሳ እህል ስለበሉ ወደ ዳኝነት ይሄዳሉ፡፡

ልጆች ሶስት ሽማግሌ አንድ ተበዳይ አንድ በዳይ በመሆን እንዲተውኑ መምረጥ፡፡ሶስቱ እንደ ሽማግሌ ሆነው የሚጫወቱት ዱቡሻ(የጋሞ ሽማግሌዎች የሚቀመጡበት ቦታ) ፊት ለፊት ይቀመጣሉ ፡፡ተበዳይ እና በዳይ ሆነው የሚጫወቱት ልጆች በሽማግሌዎቹ ግራና ቀኝ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡ሽማግሌዎች መጀመሪያ ተበዳይ እንዲናገር ያደርርጋሉ፡፡በመቀጠል በዳይ

እንዲናገር ያደርጋሉ፡፡በመጨረሻ ሽማግሌዎቹ ጠብ ጥሩ እንዳለሆነ በመግለጽ (ዮ ዮ ….በመባባል) ይቅርታ እንዲባባሉ በማድረግ የእርቅ ስርዐቱ ይጠናቀቃል፡፡

**የሚና ጨዋታ -2**

በጋሞ ባህል ሙሽሮች ቤተሰቦቻቸውን የሚጠይቁበት ባህል (ላአ)

ወንድ ሙሽራ ከጓደኛው ጋር በመሆን እሩቅ ስፍራ የሚገኙ የሚስቱን ቤተሰቦች እቤታቸው ድረስ በመሄድ የሚተዋወቅበት ስርዐት፡፡ሚስትየዋም ከአንዲት ሕጻን ልጁ ጋር በመሆን የባሏን እሩቅ ቤተሰቦች ለመተዋወቅ የምትሄድበት ባህል ነው፡፡

ይሄንን ጨዋታ ልጆች ወንድና ሴት በመሆን እንዲተገብሩት በሚና ጨዋት ማሳየት፡፡

**የስራ የሚና ጨዋታ -3**

ልጆች የስራ ባህልን በቡድን በሚያቀርባቸው ሚና ጨዋታዎች እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡የኮንሶን የእርከን ስራ በቡድን እንደጨዋታ እንዲለማመዱ ማድረግ አንዱ የስራ ሚና ጨዋታ ነው፡፡

**የተለያዩ ሙያ መስኮችን በማሳየት ሚናውን ወክለው እንዲጫወቱ ማድረግ**

ለምሳሌ የህክምናን ፣የግንበኝነት፣የአስተማሪ፣የፖሊስ ስራን እንዲገነዘቡ በማድረግ የሙያውን ባለቤቶች ሆነው እንዲተውኑ ማበረታታት፡፡እንዲሁም ማሳየት፡፡

የባለሙያዎቹን ገጸ ባህሪ በደንደብ እንዲረዱ የባለሙያዎቹን አልባሳት እና የሙያው መገልገያ መሳሪያዎችን በምስል በተደገፈ መልኩ መጀመሪያ ማሳየት ገጸ ባህሪዎቹን በቀላሉ እንዲጫወቱት ያግዛል፡፡



ምስል.4.8



ምስል.4.9

በአካባቢያችን የሚገኙ ተጨማሪ  የሙያ መስኮችን የሚገልጽ ምስል መጨመር ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ስለ ሚና መጫዎት የባህል ሚና  ለተማሪዎች ማስረዳት፡፡
- የሚጫወቱትን ሚና ከእነሱ ፈጠራ ጋር በማቀናጀት መምራት፡፡
- ድርጊቱን በከፊል ሰርቶ ማሳየት
- ተማሪዎች ሚና መተግበሩን በሚከውኑበት ጊዜ መምራት ፡፡

**4.1.3. የባህላዊ  እሴቶችን  የሚያሳዩ  ምስሎች፡**

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ስለ ባህላቸው አልባሳት እና እሴት በምስል እና ፎቶ ግራፍ ይረዳሉ
- ስለባህላቸው አልባሳት፣እጅ ስራዎች  ቀለማት ምስሎችን ያውቃሉ ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ባህልን የሚያሳዩ ምስሎች ፣ፎቶ ግራፎች
- እርሳስ ፣ላጺስ
- ለነጻ ንድፍ መንደፊያ የሚሆን ወረቀት

**ማነቃቂያ**

❖ ይሄንን ምስል በማሳየት ምን እንዳዩ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡እንዲሁም በጭፈራዎቹ መሃከል ያለውን መመሳሰል እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡
ጭፈራዎቹ ከታች የምንመለከታቸው በይበልጥ የእግርን እንቅስቃሴ በመጠቀም የምንተገብራቸው መሆኑ አንዱ የሚያመሳስላቸው ነገር ነው፡፡



ምስል.4.10 የዳሰነች ማህበረሰብ ጭፈራ

**ጠቃሚ መረጃ**

ልጆች በምስል ስለ ባህላቸው እንዲረዱ የተለያዩ የሰርግ ፣የጭፈራ፣የሽምግልና፣የአልባሳት፣የቤት አሰራር፣የእጅ ስራ እደ ጥበቦች እንዲሁም የተለያዩ ትውፊቶችን የሚያሳዩ በጉልህ የሚታዩ ምስሎችን ማሳየት ይገባል፡፡ምስሎቹ ሲመረጡ ልጆቹን አቅም ያገናዘበ እንዲሆን መምህሩ(ሯ ) ሊያስቡበት ይገባል፡፡

ልጆች የሚያዩትን የባህል ትውፊት የሚያሳዩ ምስሎችን በእርሳስ ብቻ ያለ ማስመሪያ ለመሳል እንዲሞክሩ ማበረታታት።



**ምስል.4.11** የኮንሶ ጭፈራ




ምስል.4.12 የሀመር ኢቫንጋዲ ጭፈራ

**ባህላዊ የቤት አሰራሮች**

**ለተማሪዎቹ በአካባቢያቸው እንዲሁም በሀገራቸው ያሉ የቤት አሰራሮችን በጥቂቱ እንዲመለከቱ የተለያዩ የቤት አሰራሮችን የሚያሳዩ ምስሎች ማካተት ይገባል።**



ምስል.4.16 የጉራጌ ማህበረሰብ ቤት አሰራር



ምስል.4.13 .የጋሞ ማህበረሰብ የቤት አሰራር

## የእደጥበብ ስራዎች

በአካባያችን የሚገኙ እደ ጥበቦችን እንዲያዩ ማድረግ ይገባል፡፡በእጅ የሚሰሩ ሰፌዶች ፣የሸክላ ስራ ውጤቶች፣ሽመና እንዲሁም ሌሎች የማህበረሰቡን እሴት የሚያሳዩ የእጅ ስራዎችን በፎቶ በስዕል በማሰባሰብ የበለጠ ልጆች እንዲያውቁ ማድረግ ከመምህሩ(ሯ) ይጠበቃል፡፡



ምስል.4.14 ሽመና የሚሰራ ሰው



ምስስል4.15. የእጅ ስራ ውጤት የሆኑ ስፌቶች

## የማስተማሪያ ዘዴ

- የተለያዩ ባህሎችን  የሚያሳዩ ምስሎች ማሳየት
- የባህላዊ አልባሳትን፣የእጅ ስራ ውጤቶችን ቀለማት ተማሪዎች እንዲረዱ ማድረግ
- የባህል መገለጫ የሆኑ ቀለማትን መግለጽ ፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- መምህሩ የተማሪዎችን በትክክል ምስሎቹን መረዳታቸውን መመልከት
- ልጆች ስለ ምሰሎች  መልሰው እንዲናገሩ ማድረግ
- የተመለከቷቸውን ምስሎች ለመንደፍ መሞከራቸውን መከታተል
- ስለ ምስሎቹ ቃላዊ ጥያቄ መጠየቅ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያለውን ባህል በሚና መጫወታ የባህሉን እሴት ተረድተዋል፡፡

የአካባቢያቸው የባህል አልባሳትን ቀለም እና አይነት ለይተዋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የተደረገባቸው ዋና የመማር ማስተማር ሃሳቦች፣

1.ስለ አካባቢያች ያሉ በጎ ልምድ እና ባህሎችን በሚና መጫወት እንዲሁም የባህሎቹን አንኳር ሃሰብ በተገቢው መንገድ መረዳት፡፡

2.የባህል አልባሳት ቀለም እና አይነት መረዳት እንዲሁም ማድነቅ

3. ባህላዊ መዝሙሮችን ሃሳብ መረዳት እንዲሁም ፣መዘመር እና ለባህል ሙዚቃዎች እውቅና መስጠት(ማድነቅ)

እነዚህ ከላይ የተነሱትን ተማሪ ተኮር የሆኑ የመማር ማስተማር ክንዋኔዎችን ተማሪዎች ተግባራዊ አድርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

**የቃል መልመጃዎች**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

1. በባህላችን የተጣሉ ሰዎችን ማስታረቅ ተገቢ ተግባር ነው።
2. ሃገራችን ውስጥ ብዙ የሚደነቁ ባህሎች አሉ።
3. በሃገራችን አልባሳት አንድ አይነት ብቻ ናቸው።
4. በሃገራችን የተለያየ የሰርግ ስርዐቶች አሉ።

**መልስ**

1.እውነት 2.እውነት 3.ሐሰት 4.እውነት

# ምዕራፍ -5
# ጥበባዊ ትግበራ ማቅረብ

**(ለም ሰፈፈ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-26)**

**መግቢያ**

ጥበባዊ ትግበራ በተለያዩ መንገድ ተማሪዎቹን አሳታፊ በማድረግ የሙዚቃን ፣የስዕልን ፣ የትወናን ጥበብ በአንድ የምንተገብርበት መንገድ ነው ። በትግበራው ወቅት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያዩአቸውን ልምምዶች ከአካባቢያቸው ጋር በማጣመር እንዲተገብሩ ይደረጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች**

- ለመዝሙር እንዲሁም ለጫወታ የሚሆን በቂ ቦታ ወይም ክፍል
- የድምጽ እንዲሁም የምስል ግብዐቶች
- የተለያዩ ምስሎች ፎቶግራፎች
- እርሳስ ፣ በአካባቢ የሚገኙ ባለ ቀለም መጻፊያ መሳሪያዎች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- በመዝሙር ፣በውዝዋዜ በመታጀብ ስለ ቀለም ይረዳሉ፡፡
- በቡድን ቀለል ያሉ መዝሙሮችን ይረዳሉ፡፡
- አካባቢያቸውላይ ያሉ የ ተፈጥሮ ቀለሞች መግለጽ ይችላሉ፡፡

- ቀለል ያሉ መዝሙር እና ውዝዋዜን አቀናጅተው መተግበር ይረዳሉ
- ታሪካዊ ቦታዎችን እና የተፈጥሮ ሃብቶችን የተመለከቱ መዝሙሮች ይረዳሉ በምስልም ቦታዎችን ይተዋወቃሉ፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች**

- መልዕክት በምስል ማስተላለፍ
- ጉብኝት
- የተግባር ስራ
- የተማሪዎች የግል ስራ
- ሰርቶ የማሳየት ዘዴ
- የሚሰሩትን ስራ መምራት/መከታተል
- በመዝሙር ማስጠኛ (whole song methd or phrasal song method ) ማስጠናት

## 5.1.በህብረት መዘመር

(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-8)

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- በመዝሙር ፣በውዝዋዜ በመታጀብ ስለ ቀለም ይረዳሉ፡፡
- ስለ ተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም ስለ ቀለማት የሚናገሩ በህብረት የሚዘመሩ መዝሙሮችን ያውቃሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ግብዓቶች

- ለመዝሙር እንዲሁም ለጫወታ የሚሆን በቂ ቦታ ወይም ክፍል
- የድምጽ እንዲሁም የምስል ግብዐቶች

## ማነቃቂያ

- በህብረት ሆነው  የሚችሉትን መዝሙር ማዘመር

## ጠቃሚ መረጃ


ልጆች በህብረት እንዲዘምሩ መዝሙሮቹን በሚዘምሩበት ጊዜ አንዱ አንዱን ሰምቶ ድምጽን በማስተካከል እንዲዘምሩ መርዳት፡፡

### መዝሙር

**ማን ነው ቀይ ያደረገው**

ማን ነው ቀይ ያደረገው
እኔ ነኝ ቀይ ያደረግኩት
ማን ነው ቢጫ ያደረገው
እኔ ነኝ ቢጫ ያደረግኩት
ማን ነው ነጭ ያደረገው
እኔ ነኝ ነጭ ያደረግኩት
ማን ነው ጥቁር ያደረገው
እኔ ነኝ ጥቁር ያደረግኩት

ማን ነው ቀይ ያ’ረገው



ማን ነው ቀይ ያ ረ ገው ’ኔ ነኝ ቀይ ያ’ ረ ኩት

ማን ነው ቢጫ ያ ረ ገው ’ኔ ነኝ ቢ ጫያ’ ረ ኩት

ማን ነው ነጭ ያ ረ ገው ’ኔ ነኝ ነ ጭያ ረ ኩት

ማን ነው ጥቁር ያ ረ ገው ’ኔ ነኝ ጥቁር ያ ረ ኩት

## መዝሙር

## ሃገሬን ጎብኚቼ

ተራሮችን አቋርጬ

እርሻ ማሳ ተመልክቼ

ከምንጮቹም ተጎንጭቼ

ሃይቆቹንም አይቼ

ኮ ር ቻ ለ ሁ

ሃ ገ ሬ ን

አ ይ ቼ




## የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ❖ በቡድን ማዘመር
- ❖ የተፈጥሮ ቀለሞችን ለመገንዘብ የሚረዱ መዝሙሮችን ማስደመጥ
- ❖ በቡድን እንቅስቃሴ ያለባቸውን መዝሙሮች ማዘመር

## 5.2. በህብረት ሚና መጫዎት

(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-8)

**ተማሪዎች ይሄንን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ❖ በተለያዩ ጨዋታዎች ስለ ቀለም ይረዳሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ግብአቶች

- ❖ ድምጽ ማጫወቻ (ቴፕ ፣ ሲዲ ማጫወቻ)
- ❖ በቂ ለህጻናት እንቅስቃሴ ሚሆን ቦታ

**ማነቃቂያ**

- የሚያውቁትን ጨዋታ እንዲጫወቱ ማድረግ

**ጠቃሚ መረጃ**

የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ግብዓት የቀለም አይነት እንዲረዱ ተማሪዎችን ከክፍል ውጪ አካባቢያቸውን እንዲያዩ ማድረግ ከመምህሩ(ሯ) ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪ በአካባቢያቸው ያሉ የተፈጥሮ እና የታሪካዊ መስህብ ቦታዎችን የሚያሳዩ ምስሎችን በግል ፈልጎ ለተማሪዎች ማሳየት የአስተማሪው(ዋ) ተግባር ነው፡፡

ልጆች ጨዋታዎቹን በሚያደርጉባቸው ጊዜ አካባቢያቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ የሚቻልበት ሊሆን ይገባል፡፡

## የቡድን ጨዋታ

## ቀለሟን የነካ

**አጨዋወት**

ለተማሪዎች ምቹ እና ሰፋ ያለ ቦታ ማዘጋጀት… በጨዋታው በግል ወይም እስከ አምስት ልጆችን በቡድን መምረጥ ፡፡መምህሩ የአንድ ቀለም ስም ሲጠራ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙን መምህሩ የጠራው ቀለም አይነት የያዘ ቁስ በቶሎ በመንካት ያሳያሉ፡፡ ቶሎ ቀለሙን የነካ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

በስተመጨረሻም ለሁሉም ተማሪዎች ማበረታቻ በጭብጨባ መግለጽ፡፡

**የቀለም የቡድን ጨዋታ**

ልጆች ሶስት ወይም አራት በመሆን የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ አንድ ልጅ ጨዋታውን እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ጨዋታውን የሚመራው ልጅ ጨዋታውን

አረንጓዴ፣አረንጓዴ እያለ ይዘምራል

የሚጫወቱት ልጆች አረንጓዴ ሲባል ባሉበት ዱብ ዱብ ይላሉ ፡፡ድንገት ቢጫ ሲል ይቀመጣሉ፡፡ቀይ ሲል ቀጥ ብለው ይቆማሉ፡፡ የጫዋታውን መሪ ልጅ በመከተል ይተገብራሉ ፡፡ያልታዘዘውን ያደረገ ልጅ ጨዋታውን ይፎርሻል፡፡ለምሳሌ ቀይ ሲባል የተቀመጠ ወይም ዱብ ዱብ ያለ በጨዋታው ይፎርሻል፡፡

## 5.3. ስለ ተፈጥሮ ሃብት እና በዙሪያችን ስላሉ የተፈጥሮ ቀለሞች

**ከመዝሙሮች እና ምስሎች ጋር አቀናጅቶ መተግበር**
**(ለርዕሱ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ-10)**

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- ❖ አካባቢ ላይ ያሉ አበቦችን ፣አትክልቶችን፣ፍራፍሬዎችን ቀለም ይረዳሉ
- ❖ ስለተፈጥሮ የሚያወሱ መዝሙሮችን ይዘምራሉ
- ❖ ስለ ተፈጥሮ ሀብት ይገነዘባሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ግብዓቶች

- የተለያዩ እንሰሳትን ፣ የተፈጥሮ ቦታዎችን መልካ ምድሮችን የሚያሳዩ ምስሎች
- አካባቢያቸውን ለመረዳት የሚሆን በቂ ስፍራ ከክፍል ውጪ

## ማነቃቂያ

- ከዚህ በፊት የሚያውቋቸው ስለ ዛፎች ስለ ቀለሞች የተዘመሩ መዝሙሮች ካሉ እንዲዘምሩ ማድረግ

## ጠቃሚ መረጃ

ልጆች አካባቢያቸው በማየት ስለተፈጥሮ እንዲገነዘቡ ከክፍል ውጪ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ከተቻለም በአካባቢያቸው በመውሰድ የተለያዩ የተፈጥሮ ነገሮችን በማየት ቀለማትን እንዲማሩ ማድረግ ከመምህሩ(ሯ) ይጠበቃል፡፡



ምስል.5.1

ወንዙ፣ ሰማዩ ፣ዛፎቹ ፣ሳሩ ቅጠሉ የተፈጥሮን ቀለማት ያሳዩናል

**የእንስሶችን ን የቆዳ ቀለም በማሳየት**



ምስል.5.2



ምስል.5.3

**የአእዋፋትን ቀለማት ማሳየት**



ምስል.5.4

## የአበባ ቀለማትን የያዙ ምስሎን ማሳየት



ምስል.5.5

## የአትክልትና የፍራፍሬ ቀለማትን ማሳየት



ምስል.5.6

## ስለ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ሃብቶች

በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶችን ማሳየት ስለ አካባቢው ቀለም ማሳየት ፡፡

ወንዞችን ፣ተራሮችን፣ሃይቆችን በምስል ማሳየት

ሰው ሰራሽ ቦታዎችን ለምሳሌ የኮንሶን የእርከን ስራ፡፡



ምስል.5.7. የጫሞ ሃይቅ

**የመማር ማስተማሪያ ክንውኖች**

- ❖ አካባቢን ማስቃኘት፡፡
- ❖ የተፈጥሮ ቀለሞችን ለመገንዘብ የሚረዱ መዝሙሮችን ማዘመር፡፡
- ❖ ስለ ተፈጥሮ ቀለማት እንዲሁም ገጽ የሚያሳዩ ምስሎችን ማስመልከት፡፡
  አትክልቱን፣ፍራፍሬውን ፣ተራራውን፣እንሰሳውን፣አእዋፉን ማሳየት፡፡
- ❖ የተማሪዎች መጽሀፍ ላይ ያሉትን ምስሎች በመጠየቅ ልጆች ስለቀለሞቹ እየሞከሩ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**ግምገማ**

- ❖ ተማሪዎች አካባቢያቸውን መገንዘባቸውን መመልከት
- ❖ ስለተፈጥሮ ቀለሞች በግል እና በቡድን እንዲናገሩ ማድረግ
- ❖ ስለተፈጥሮ ቀለማት የቃል ጥያቄ መጠየቅ

❖ በተማሪዎች መማሪያ መጽሃፍ ላይ ያሉ  የቃል ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማበረታታት፡፡

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ስለ አካባቢያቸው በማወቅ ስለ ቀለሞቻቸው  መዝሙሮችን በማካተት ተግብረዋል፡፡ ተፈጥሮአዊ ሃብቶች እንዲሁም

የተለያዩ በአካባቢያችን ያሉ ሃብቶችን እንዲመለከቱ እና እንዲቃኙ ተደርጓል፡፡

በአካቢቢያቸው የሚገኙ አትክልቶችን ፍራፍሬዎችን በማሳየት ስለ ቀለሞቻቸው እንዲሁም ስለ ቅርጻቸው በጥበባዊ እይታ እንዲገነዘቡ ተደርጓል፡፡

በዚህም ምዕራፍ ከቀለማቸው ባለፈ አካበቢያቸው ላይ ያሉ እንሰሳቶችን ፣ አእዋፍትን በምስል ማስቃኘትም ተችሏል፡፡

**የቃል መልመጃ**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች  መልስ ስጡ**

1. በአካባቢያችሁ ካሉ የተፈጥሮ ቀለማት  የምትወዱት ቀለም ምንድን ነው?
2. በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ  በብዛት ያሉት ቀለሞች ምንምን ናቸው ?
3. ስለ አካባቢያችሁ የሚናገር አንድ መዝሙር ዘምሩ ?

## ዋቢ መጽኃት


Ganet mills - Music in the primary school

Rhona whitaford and Fitzimmon -Music and movement

Wilson.Ehret -Growng with music (5)

Herman.renna